# ፍካሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
ታትሞ የሚወጣ

## ጥናታዊ የትንተና መጽሂት

## በኢትዮጵያ የብሔረሰብ ክስተት

## ልዩ እትም

ቅጽ 16 ቁጥር 1 መስከረም 2001 ዓ.ም.

# ስለ ፍካሬ ልታውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮች

በፍካሬ የሚወጡ ጽሁፎች ሁሉ የፓርቲ አባላት የጻፏቸው ጽሁፎች ወይም የፓርቲው አቋሞች አይደሉም። የፓርቲውን አቋም የሚመለከት ጽሁፍ ሲወጣ ይህንን ያስታውቃል።

1. የሚላኩ ጽሁፎች በአማርኛ የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል።

2. የአመት ደንበኞች ለመሆን የሚሹ ሁሉ አመታዊ ክፍያው ለአራት ዕትሞች 16.00 ኦይሮ ወይንም ደግሞ ተመጣጣኝ ምንዛሬ ይሆናል። ይህንኑ በፖስታ ሳጥን ቁጥራችን መላክ ይቻላል። የሚከፈለው በቼክ ወይም በመኒ ኦርደር ለኢ.ሕ.አ.ፓ ነው።

3. ፍካሬ በአመት አራት ጊዜ ትወጣለች።

4. ጽሁፎች መላክ የሚፈልጉ በሀገራዊና አለም አቀፋዊ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጉዳዮች፣ ሥነ ጽሁፎችና ፓርቲ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ሊላክልን ይቻላል። በተቻለ መጠን ጸሃፊዎቹ ስማቸውን አለዚያም የብዕር ስማቸውን ሊነግሩን ይገባል። የብዕር ስም የሚጠቀሙ ከሕጋዊ እርምጃዎች አንጻር አግባብ ስላለው ለአዘጋጆቹ ብቻ ስማቸውንና አድራሻቸውን መግለጽ ይኖርባቸዋል።

5. ጽሁፎች እስከተቻለ ድረስ በጣም ባይረዝሙ (ከ 5-7 ገጽ) ባይበልጡ ይመረጣል። ለጥራትና ለመጠን ሲባል ጽሁፎች እርማት ሊደረግባቸው ይችላል።

6. የሚደርሱንን ደብዳቤዎች በየጊዜው እናወጣለን። ደብዳቤ የሚጽፉ ስማቸውንና አድራሻቸውን ከነስልክ ቁጥራቸው በትክክል እንዲያሰፍሩ እንጠይቃለን።

7. ርዕሰ አንቀጾቹ ከዝግጅቱ ክፍል የሚቀርቡ ናቸው።

ዋና አዘጋጅ ዶ/ር ዘነበ ተሾመ

ምክትል ዋና አዘጋጅ ሀይሉ ወንዴ

መጽሂቷን ለሚመለከቱ ግንኙነቶች በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ።

FIKARE
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A

# ፍካሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

ታትሞ የሚወጣ

ሩባዊ መጽሄት

## ርዕሰ አንቀጽ

የኢትዮጵያ ሀገራችንን ሕልውና ጽኑ መሰረት ባለው መንገድ በዘላቂነት ለማስጠበቅ ብሎም የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ የማህበራዊና የተቀሩትንም የተለያዩ ችግሮች ውል ባለው ዘይቤ እንዲፈቱ የዴሞክራሲ አካል የሆነው የብሔር/ብሔርሰቦች ጥያቄ በአግባቡ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ኢሕአፓ በተለያዩ ጊዜያት ከፍተኛ ቅስቀሳ ያደረገበትና በርካታ ጥናታዊ ጽሁፍም ሆነ መግለጫዎች ያሰራጨበት መሆኑ ይታወቃል። ይህንን ቀና አስተሳሰቡን በክፉ አይን የተመለከቱና ድርጅቱንም በጥላቻ የወሰዱ ትምክህተኞችና ጠባቦች ከፍተኛ ውግዛ ብቻ ሳይሆን ሕልውናውን የተፈታተነ የጥፋት እርምጃ ወስደውበታል። በርካታ አባላቱና ደጋፊዎቹ የሕይወት መሰዋዕት ከፍለውበታል። አሁንም እየከፈለ በት የሚገኝ ነው። ጥያቄው ከተነሳና ማወያየት ከጀመር ጊዜ አንስቶ መፍትሄ ሳይሰጠው ይኸው እየተንከባለለ ለጥቂቶች በተለይም የጎሳን ፖለቲካ ለሚያራምዱ፣ የሀገርንና የወገንን ጥቅም እንዲሁም ፍላጎት ወደጎን ለሚያደርጉ ዘረኛና አምባገነኖች የስልጣን መረማመጃ ሆኖ ሕዝብን እያመሰቃቀለ ይገኛል። ይህ ርዕስ በኢትዮጵያ ዜጋ አማካይ የእድሜ ዘመን ቢለካ እንኳ የአንድ ትውልድ እድሜ አስቆጥሮ ወደ ሌላው ለመሸጋገር የሚቀረው በጣም ጥቂት ነው። አሁንም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለችግሩ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት በተለይም ለማህበራዊ ሰላም ምቹነት ያለው መፍትሄ ካልተሰጠው ሁኔታዎቹ እየተባባሱ በመሄድ ዘላቂ መፍትሄ የማግኘቱ ሃላፊነት በተተኪው ትውልድ ጫንቃ ላይ መውደቁ የማይቀር ነው። የታሪክ ሂደት እንደተፈለገው አይቀመርምና ይህ ሆነ አልሆነም የወደፊቱንም ሆነ የወቅቱን ሁኔታ ከግምት በማስገባት ለጥያቄው አሁንም በቂ ትኩረት ሰጥቶ የጋራ ግንዛቤ አስገኝቶ መንቀሳቀስና ሕዝብንም በዚህ ዙሪያ ማታገል አግባብነት ያለው መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

ለዚህ በተለይ በደርግና በተለይም በወያኔ ዘመን የተወለደ ኢትዮጵያዊ ተኪ ትውልድ ነውና የችግሩን እምብርት ከወቅቱ ሁናቴ ጋር በማገናዘብ መፍትሄ እንዲሰጥ ለማስቻል በቅድሚያ ያለፈውን የትግል ታሪክ በጥሞና ሊረዳ ይገባል። የእድሜ ባለጸጋ ሆነው በሶስቱም የአገዛዝ ሥርአት በትግል ውጣ ውረድ ለማለፍ የቻሉ ሀገር ወዳድ ታጋዮች

በርካታ ተመክሮ ያካበቱ ናቸውና ለዚህ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ተተኪውን ትውልድ ሁኔታውን በሚገባ የማስጨበጥ ሀገራዊ የዜግነት ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው። ለዚህ ደግሞ በተለያየ ደረጃና አኳኋን የብሔር/ብሄረሰቦችን ጥያቄ በኢትዮጵያ ለምን ማንሳት አስፈለገ? ጥያቄውን አስመለክቶ በድርጅቶች መሀል የታየው ልዩነት ምን ይመስል ነበር? አሁንስ መልኩን ቀይሯል ወይንስ አልቀየረም? ከቀየረስ መፍትሄው ምን ይመስላል? በተለይ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን


ከመያዙ በፊትና በኋላ በዚህ ጥያቄ ላይ ያራምደው የነበረውና አሁን ይዞት የሚንቀሳቀስበት ፖለቲካ ምን ይመስላል? በይበልጥ ደግሞ በኤርትራ ይከተለው የነበረው ፖሊሲና ያስከተለው ጣጣ በቅርቡ ደግሞ ከምዕራብ ኢትዮጵያ በጣም ለም የሆነ የመሬት አካባቢን ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት ከሱዳን መንግሥት ጋር ውስጥ ውስጡን ሲደራደር ከርሞ የተጋለጠበት ሁኔታ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? የባዕዳን አጀንዳን ለማስፈጸም የወያኔ አገዛዝ በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከገባ ጊዜ ጀምሮ እያደረጋቸው ያላቸው ኢሰብአዊ ድርጊቶች በሀገራችን ሕዝብ ላይ እያስከተለ ያለው ጉዳትን ለማስቆምና በአካባቢው ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋትን አስገኝቶ ወደ እድገት ጎዳና ለመጓዝ እንዴት ይቻላል? ብሔራዊ አንድነትና የሀገር ሉአላዊነት ከብሔር ጥያቄ ጋር ያለው ምን መልክ ይኖረዋል? እና ሌሎችም ጥያቄዎችን አንስቶ በጥልቀት መተንተንና ማስረዳት የሚጠበቅ ነው።

በአሁኑ የፍካሬ እትማችን በተለያየ ደረጃ አሁንም ድረስ ኢትዮጲያዊያንን እያነጋገረ፤ አንዳንዴም ጎራ እያስያዘ የሃሳብ ፍትጊያ እያስከተለ ያለ አንድ የፖለቲካ ርዕስ ቢኖር የብሔር/ብሔረ)ሰቦች ጥያቄና መፍትሄውን የሚመለከት ነው። ይህንን አስመልክቶ አንድ ሰፋ ያለ ጽሁፍ ቀርቦልን የጥያቄውን አንገብጋቢነትና በወያኔ የበላይነት ጠባቦችና ዘረኞች በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች በተለይም በምስራቅ፤ በሰሜን ደቡብና በደቡብ የሀገራችን ክፍሎች እያካሄዱት ያሉት እንቅስቃሴ ለበርካታ ዜጎቻችን ለእልቂት መዳረግ፤ የሕዝብ ሀብትና ንብረት መባከን፤ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸው መፈናቀልና መሰደድ፤ የሀገር ሉአላዊነት መደፈርና የሕዝብ አንድነት መናጋት ሕዝባችንን ከምንጊዜውም በላይ ወደከፋ ደረጃ የሚወስድ የርስ በርስ እልቂት እያዘጋጁት በመሆኑ በልዩ እትም ደረጃ እንዲወጣ አድርገናል። ይህንንና በተለይም ደግሞ የኢ.ሕ.አ.ፓ 36ኛ ምስረታ በመላ አለም የሚከበርበት መሆኑን ከግምት በማስገባት ድርጅቱ በዚህ ጥያቄ ላይ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በተከታታይ ያስተጋባውንና

እያስተጋባ ያለውን አቋም ለመረዳት የሚያስችላቸው በርዕሱ ላይ የሚኖራቸውን እውቀት ለማዳበርና ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ይጠቅማል ብለን እንገምታለን። ስለሆነም ይህንን ጽሁፍ አንባቢያን በጥሞና እንዲያነቡት እንጋብዛለን።

ሀገራችን አሁን ከገባችበት ማጥ እንድትወጣ መቀየስ ያለበት መርህ ምንድነው? ሕዝብን ሊያስማማ፤ ሊያቀራርብና ለእድገቱ መሰረት ሊሆን የሚችለውስ ጎዳናስ ምንድነው? ለነዚህ ጥያቄዎች ከሀገር ወዳድ የፖለቲካ ሃይሎች፤ ከሲቪሉ የማህበረሰብ ክፍሎች፤ ከሀገር ወዳዱና ከወገን አፍቃሪውስ የሚጠበቀው ምን አይነት አስተዋጽኦ ነው? በነዚህም ሆነ በሌሎች አበይት ጥያቄዎች ላይ ደራሲዎች ያሏቸውን አስተያየቶችና ግንዛቤያችንን የሚያዳብሩ መጣጥፎችን እንዲያበረክቱ ፍካሬ ጥሪዋን ታቀርባለች። የጋራ ግንዛቤ እንዲገኝ ፍካሬ የውይይት መድረክ ሆና
ለማገለገል የታቀደች ናትና አንባቢያን የቀረቡትን ጥያቄዎች ከብሔር/ብሔረሰብ
ችግር ጋር በማያይዝም ሆነ በተናጠል አንድ ቢሉ ኢትዮጵያን ከውድቀት ሕዝቧን ከእልቂት ለማዳን የመጀመሪያው እርምጃ ይሆናል። ሰው ያለውን ከወረወረ የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው ይህንኑ ነው።

መልካም ንባብ እንመኝላችኋለን!!



## በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ክስተት

ኢትዮጵያ በረጅም የታሪክ ሂደት የተለያዩት ብሄረሰቦቿ መልካሙንና ክፉውን ጊዜ አብረው በማሳለፍ የጋራ የሆኑ እሴቶችና አንድነት ማለት ኢትዮያዊነትን ፈጥረዋል። ኢትዮጵያዊነት ስንል በአገሪቱ የሚገኙ ብሄረሰቦች፣ ሀይማኖቶች፣ ባህሎችና ቋንቋዎች ለብዙ ሺ አመታት አብረው በመኖርና በመዋለድ በጋራ ያዳበሩትን የአንድነት

መግለጫቸውን ማለት እንደ ድርና ማግ የሚያስተሳስራቸውን ማለታችን ነው።

በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ጉዳይ አዲስ የመጣ ወይም የተፈጠረ ክስተት ሳይሆን ያለና የነበረ ችግር ነው። በመሆኑም የችግሮቹን መጠንና ዓይነት፡ አግባብነት ያላቸውና አግባብነት የሌላቸውን በመለየት አግባብነት ላላቸው ችግሮች የመፍትሔ አሳቦች መፈለግና ምርመር ማድረጉ ላይ ማተኮሩ ጠቃሚነት አለው ብለን እናስባለን። ትግላችን በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወስን መብት ማክበርና እኩልነታችንን በማስረግጥ የሁላችን የምትሆን ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሪፓብሊክ መመስረት ነው።

## <u>የኢትዮጵያ አገራዊ አመስራረትና አስተዳደር</u>

የአገራችን የኢትዮጵያ ታሪካዊ አመስራረትና አስተዳደር ብዙ ሺ አመታት የሚዘልቅ በመሆኑ ርዕሳችን የሚያብራራልንን ለይተን በአጭሩ ጥንታዊና ዘመናዊ ኢትዮጵያ አመስራረት ብለን እናቀርባለን። በእኛ በኩል የጥንታዊ ኢትዮጵያን ታሪክ፡ አስተዳደርና ሥርዓት እንዲሁም አኗኗርና ባህሎች በተሟላ መልክ ለማቅረብ መሞከር "አባይን በጭልፋ" ስለሚሆንብን ለታሪክ ተመራማሪዎች መተውን መርጠናል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ታሪክ ትተን ከዚያ በኋላ ያለውን አመታት ብንወስድ እንኳን ይኸው ዘንድሮ የ2000 አመት (millennium) ለማክበር መቻሉን እንገነዘባለን።

የጥንት ታሪኮችና ስልጣኔዎች እንዲሁም የሰው ዘር አፈጣጠር ወይም አመጣጥ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች (historians, archaeologists, anthropologists and paleontologists) እንደሚሉት ከድንቅነሽ ግኝት ባሻገር፤ የሰው ዘር ምንጩ ኢትዮጵያ ናት ወደሚለው አዲስ ንድፈ አሳብ እያመሩ ይገኛሉ። ተመራማሪዎቹም የሰው ዘር ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ ቀረው ዓለም ፈልሷል የሚል አስተሳሰብ እያቀነቀኑ ነው። ታዲያ የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ያለመታደል ሆኖ የኋልዮሽ በመሄድ በዘረኛው ወያኔና በተለጣፊዎቹ መሰሪነትና ቀስቃሽነት አንድነታችንና ታሪካችን በማንኳሰስ፡ ልዩነታችንን በማጋነን ወደ ዳግማዊ ዘመነ መሳፍንት በማምራት ላይ መሆናችን ነው።

ወደ ዘመናዊ የኢትዮጵያ አገር ግንባታና ሥርዓት በቀጥታ ከመሸጋገራችን በፊት እንደመንደርደሪያ (background) የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያን ሁለት መጻሕፍት **"የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ 1500-1800"** እንዲሁም **"የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ"** እንድንገመግም ይፈቀድልን። የጥንታዊ የንጉስ ነገሥት አስተዳደር ማለት በፌደራላዊ መዋቀር፡ ውስጥ እንዴት የተለያዩ ሃይማኖቶችና ብሄረስቦች ተቻችለው አብረው ለመኖር ቻሉ? በኋላስ የማዕከላዊ ፌደራል መንግሥትስ እንዴት ተዳከመ? እንዴትስ የራስ አገዛዝ የነበሩት የትንንሽ ንጉሦች/ራሶች በማዕከላዊ መንግሥት ላይ የበላይነትን ለማግኘት ቻሉ? የዘመነ መሳፍንት ጠንቅ ወይም ጦስ ያመጣው የፖለቲካ፡ የኤኮኖሚና የሶሻል እንደምታዎች ምን ነበሩ? በአፄ ቴዎድሮስ የተጀመረው የማዕከላዊ ንጉስ ነገስት እንዴት በአፄ ሃይለ ሥላሴ ወደ ፍጹም የማዕከላዊ አስተዳደር ተቀየረ? በአሁኑ ወቅት ደግሞ ዳግማዊ ዘመነ መሳፍንት በራችን እያንኳኳ በመሆኑ እንዴት ልንታገው ይገባል? ማለትም የአገራችንን አንድነትና ህልውና የብሄረስቦችን መብት ለማስጠበቅና ለማስከበር ምን ማድረግ አለብን? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመፈለግ አንዳንድ ፍንጭና እንደምታ ስጪ አስተሳስቦች ከመጻሕፍቱ ፈልፍለን ለማውጣት ጥረት አድርገናል። የጽሁፋችን ዋናው ዓላማ ለወጣቱ ትውልድ ለጥናታዊ ትምህርትና ምርምር በሚያመቸው መንገድ ለማቅረብ የአቅማችንን አስተዋፆ ለማድረግ ነው። ሌላው ፍላጎታችን የነገስታት ገድሎችን በማተት ለማሞገስ ወይም ለመኮነን ሳይሆን በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ የነበረውን የሕዝባችንን አኗኗር፡ ባህል፡ አስተሳስብና እምነት ምን እንደሚመስል ለወጣቱ ትውልድ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንደሆነ ይታወቅልን። በዚህ አጋጣሚ ለወጣቶች አደራ የምንለው የአርቲስት ወጋየሁ ንጋቱን ትረካ **"ፍቅር እስከ መቃብር"** በአቶ አዲስ አለማየሁ የተጻፈውን ሲዲ (CD) ገዝታችሁ እንድታዳምጡ ነው።

አንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች በአገራችን የነበረውን የጥንታዊ ፌደራላዊ ሥርዓትን የፊውዳላዊ ፌደራል ሥርዓት (fuedo-federalism) ብለው ይጠሩታል። የንጉስ ነገስት አስተዳደር ማለት አንዱ ጠንካራው የስለሞን ዘር ያለው ንጉስ የማዕከላዊ መንግሥት አስተዳዳሪ በመሆን በውስጡ የራስ አገዛዝ ሥልጣን ያላቸው ትንንሽ ንጉሦች፡ እራሶችና ባለሌላ ማዕረግ ያላቸውን ያካተተ ሥርዓት ማለት ነው። ለአብነት አንዳንዶቹን የራስ አገዛዝ የነበራቸውን ለመጠቃቀስ የሸዋ ንጉስ፡ የጎንደር ንጉስ፡

የወሎ ንጉስ፡ የትግሬ ንጉስ፡ የጎጃም ንጉስ፡ የዋግ ሹም፡ የአፋርና የሐረር ሱልጣኖች፡ የጅማው አባጅፋር፡ የወለጋው ጆቴ፡ የወላይታ ንጉስና የከፋ ንጉስ እንዲሁም ባሕረ ነጋሽ ወዘተ...ነበሩ። ትንንሽ ንጉሦቹ ከማዕካላዊ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ያሙት ግብርና ገፀ በረከት ለዋናው ንጉስ ነገሥት መስጠት፡ በጦርነት ጊዜ ንጉስ ነገስቱ ክተት ሠራዊት ብሎ ነጋሪት ሲያስጎሽም በተባለው ቦታና ቀን ስራዊታቸውን ይዘው መገኘት ግዴታቸው ነው። ንጉስ ነገሥቱም እራስ አገዛዦች በውጭ ወራሪ ጠላት እንዳይጠቁ የመጠበቅ ሃላፊነትና እንዲሁም በችግራቸው ጊዜ
ማለት ርሃብና ተፈጥሮ ስራሽ ችግሮች ሲያጋጥማቸው የመርዳት ግዴታ ነበረበት። እንዲሁም በትንንሽ ንጉሦች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ዳኝነት ይስጣል፡ ያስማማል። ንጉስ ነገሥቱ ዋና መናገሻ ከተማ ቢኖረውም ለምሳሌ የጎንደር ቤተ መንግሥት ዓይነት አብዛኛውን ጊዜ የማዕከላዊ ንጉስ የሚያሳልፈው በአገሩ ውስጥ በመዘዋወር ፀጥታን በማስከበር፡ ዳኝነት በመስጠት፡ ግብር አንስጥም ያሉትን በመቅጣት በድንኳን በተለያዩ ቦታዎች በመንከራተት ነበር። ከንጉሱ ጋር አብሮ የሚዘምተው ወይም የሚጓዘው ስራዊት የወር ደሞዝተኛ ባለመሆኑ ሁሉንም ነገር ማለት ማብላትና ማጠጣት አላፊነቱ የገበሬው ነበር። ንጉሱም አንድን ቦታ ነቅሎ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ አካባቢው ልክ በአንበጣ መንጋ እንደተጠቃ ምድረበዳ ነበር የሚሆነው። በገበሬውም ላይ የሚደርስው በደል እልቆ መሳፍርት ነበረ። አሁንም በዘመናችን መልኩ ይቀያየር እንጂ በአርሶ አደሮች ላይ የሚደረስው በደል በከፋ መልኩ እንደቀጠለ ያለ ነው።

ለፌደራል ማዕከላዊ መንግስት ማለት ንጉስ ነገስት መዳከምና የዘመነ መሳፍንት መምጣት በዋናነት የሚጠቀሱት የብሄረስብ፡ የሃይማኖት ግጭቶችና የውጭ አገሮች ጣልቃ ገብነት ናቸው ማለት ይቻላል። በዚያን ዘመን የነበሩት ሃያላን መንግሥታት ፖርቹጋልና ቱርክ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በኢትዮጵያ በክርስቲያንና በእስልምና ተከታዮች መካከል ለሥልጣንና የአገሪቱን ሀብት ለመቆጣጠር በተደረገው ጦርነት 1506-1543 ብዙ ሕዝብና ንብረት እንዲወድም ምክንያት ሆነው ነበር። በጦርነቱም ፖርቱጋል መንግስት ለክርስቲያን ንጉስ አፄ ልብነ ድንግል እንዲሁም የቱርክ መንግስት ለእስልምና መሪው ኢማም አህመድ መሀመድ በተለምዶ “ግራኝ መሀመድ” ደጋፊ ሆነው በመቅረባቸው የእርስበርስ ጦርነቱ እንዲባባስ አድርገዋል። ከዚያም የኢማም አህመድ መሀመድ የስልጣን ዘመን አክትሞ እንደገና

ስለሞናዊ ንጉስ ነገስቱ አገር መግዛት ቀጠሎ ብዙም ሳይቆይ በካቶሊክና በኦርቶዶስ ተከታዮች መካከል ሌላ ብጥብጥ ተነስቶ ብዙ ሕዝብ ለማለቅ በቅቷል። አፄ ሱስንዮስ በጊዜው ሃያል የነበረውን የእስፔን መንግሥትን እርዳታና ድጋፍ ለማግኘት የካቶሊክን እምነት በመቀበሉ ብዙ የኦርቶዶክስ ተከታዮችና ቀሳውስቱ እንዲሞቱና የተረፉቱም ለስደት ተዳርገዋል። አፄ ሱስንዮስ ሲሞቱ በምትካቸው ልጃቸው አፄ ፋሲል የኦርቶዶክስ ተከታይ የሆነው ነገሱ። በእንደዚህ ያሉ ፍትጊያዎችና ግብግቦች ማለት የሃይማኖቶች ግጭቶችና በንጉስ ነገስቶችና በመሳፍንቶች መካከል በሚደረገው ፉክክር ሁሉም የበኩሉን አሸናፊ ለመሆን ብዙ ጥረቶች ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ አፄ በካፋ ስልጣኑን ለማጠናከር ኦሮሞዎችን ፍለጋ እስከ ግንደበረት ድረስ በመዝለቅ የሜጫና ቱለማ ኦሮሞዎችን አምጥቶ በባህር ዳርና በጎንደር ደንቢያ አውራጃ መሬት ሰጥቶ አስፍሯቸው ነበር።

ኦሮሞዎች በፈረስና በጩበጣ ውጊያ ጎበዞችና ጀግና ስለነበሩ ለንጉስ ነገስቱ በስልጣን ለመቀጠል ዋስትና ስጪ ሆነው ነበር። በመሆኑም በዘመነ መሳፍንት ዋዜማ
ኦሮሞዎች በቤተ መንግስት ከተራ ወታደር እስከ የጦር አለቃ ከዚያ አልፎ በዘመነ መሳፍንት የንጉስ እንደራሴና ሞግዚት ማለት እንደነ ራስ አሊ ለመሆን በቅተው ነበር። ነገር ግን የኦሮሞ የገዳ ሥርዓት የመሳፍንቱን መጠናከርና የማዕከላዊ መንግስትን መዳከም ሊገታውና ሊያቆመው አልቻለም ነበር። የንጉስ ነገስቶች ሥልጣን ቀስ በቀስ በሂደት እየተሸረሸረ መጥቶ በመጨረሻ በአፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን የማዕከላዊ ፌደራላዊ ንጉስ ነገሥት ተፈጸመና የእራስ አገዛዝ መሳፍንት የበላይነትን ያዙ።

## *ዘመነ መሳፍንት*

ዘመነ መሳፍንት ማለት የማዕከላዊ መንግሥት ያከተመበትና ትንንሽ ንጉሶች በየቦታው እርስበርሳቸው የሥልጣንና የሀብት ባለቤት ለመሆን በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ የነበሩበት ጊዜ ነው። የዘመነ መሳፍንት ዋና ተዋንያን የነበሩት የአገው፡ የኦሮሞ፡ የላስታ፡ የአማራው፡ የሸዋው፡ የትግሬው፡ የጎጃሙና የጎንደሩ ወዘተ... ትንንሽ ንጉሶችና ራሶችና ባለሌላ ማዕረግ መሳፍንት ነበሩ። አንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች ይኸን ዘመን የጨለማው፡ የሽብርና የመበታተን ጊዜ ብለው ይጠሩታል። ዘመነ መሳፍንትን አስመልክቶ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በመጻሐፋቸው በገጽ

290 ላይ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡ “ሁሉም በያውራጃው እንደ ንጉስ ሆነ፡ አንዱም ባንዱ ላይ ሥልጣን አግኝቶ ሊያዘው አልቻለም። በበጌምድር ትልቁ ራስ ዐሊ፡ በዳሞት ራስ ክፍለ አዳም፡ በትግሬ ራስ ክፍለ ኢየሱስ፡ በፊት ቀጥሎ ልጃቸው ራስ ወልደ ሥላሴ ይገዙ ገሥመር። ሸዋም ገና አስቀድሞ ከአፄ ኢያሱ ብርሃን ስገድ ዘመን ጀምሮ ተነጥሎ በዚህም ዘመን እስፋ ወስን መጀመሪያ ወስን ስገድ ተክትለው ራሳቸውን ችለው ሸዋን ያስተዳድሩ ነበር።”

በጎንደር ቤተ መንግሥት በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ነገስታቱ የስለሞን ዘር ያላቸው ብቻ በመሆናቸው አገር ያረጋጋሉ፡ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት (legitimacy) አላቸው በመባል ዘውድ ጭነው በቤተ መንግስት እንዲቀመጡ ተደርጎ ነበር። ከዚያ ባሻገር ምንም የመሾምና የመሻር ስልጣን አልነበራቸውም። በቤተ መንግስቱም ውስጥ ንጉሶች የሚታዩት እንደ አሻንጉሊት ነበር። ተመርጠው የሚመጡት ማለት በእንደራሴዎች ከመሳፍንት አምባ ከሚባል ቦታ፡ ማለት የስለሞን ዘር ያለባቸው በቁም እስረኛነት የሚታጎሩበት ስፍራ ነበር። አምባው ዙሪያውን በተራራ የተከበበና አንድ በጥብቅ የሚጠበቅ በር ያለው ስፍራ ነው። አምባው የተቆረቆረው ከዘመነ መሳፍንት በፊት በንጉሳዊያን ቤተስብ የስልጣን ሽኩቻና ግብግብ ስለ ነበር ንጉሱ ወንድሞቹን፡ አጎቶቹን፡ አንዳንዴም ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጆቻቸውን ሥልጣን ይቀሙናል የሚል ፍራቻ ስለ አለ በአንባው ውስጥ እንዲቀመጡ ያደርግ ነበር። ለማስታወስ በእኛ ዘመን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ስንውስድ አንድ የሚጠናና በፈተና ጊዜ ይመጣል ተብሎ የሚገመተው አማርኛው ወልጋዳና ከባድ
የሆነ “እራሴላስ” የሚባል መጽሐፍ ነበር። ወጣቶች ይኸን ስዕላዊ ልብ ወለድ የመሳፍንት አምባ መጽሐፍ አግኝታችሁ ስለአምባው አቀማመጥና አስተዳደር ግንዛቤ እንድታገኙ ፈልጋችሁ እንድታነቡት እንመክራለን።

በእኛ ግምት አገራችን በእድገት ወደኋላ እንድትቀር ወይም እንድትጎተት ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ በዘመነ መሳፍንት የዳበረው ጎጂ ባህሎች ማለት ጠመንጃ ያነገበው ማለት የንጉሱ እንደራሴ አሽከሮች/ወታደሮች የተከበሩበት ገበሬው፡ ቀጥቃጩና እንጥረኛውና አዝማሪው የተናቁበት ማለት የሚስራ የተናቀበት የማይስራው የተከበረበት ዘመን በመሆኑ ነው። እንዲህ ያሉ ጎጂ ባህሎች የእራስ

አነሳሽነትና የፈጠራ ሥራዎች እንዳይዳብሩ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር ማለት ይቻላል።

በዚህ የመሳፍንት ትርምስ ዘመን በነገስታቱ ስም በሞግዚትነት የንጉሱ እንደራሴ በመሆን አገራችን ከ75 አመት በላይ ገዝተዋል። መሳፍንቱም ቢሆኑ ለጊዜው እንጂ አንፃራዊ ሰላም አግኝተው አያውቁም ነበር። አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት የሚነሱባቸውን ተቀናቃኞች ማለት ከትግሬ፡ ከጎጃም፡ ከላስታ፤ ከአማራና ከኦሮሞ ራሶችና ባላባቶች ጋር በተናጠልና በቡድን ጦርነት በማካሄድ ነበር። የዋንኞቹም የዘመነ መሳፍንት እንደራሴዎች ከአንድ ቤተሰብ ከስምንት የማይበልጡ ነበሩ። ዝርዝር ስማቸው ለማወቅ ለምትፈልጉ በዋቢዎች ገጽ ላይ ያለውን ይመልከቱ።

ዘመነ መሳፍንትን ለመቋጨት ሃይማኖቶቹ በአገራችን የተጫወቱን ሚናዎች በአጭሩ እንድናቀርብ ይፈቀድልን። በኢትዮጵያ የሃይማኖቶች በተለይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ከመንግሥት ጋር የነበራቸው ቁርኝት ከፍተኛና ጥብቅ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ስዎች/ሊቃውንት ግዕዙን በደንብ ስለሚያውቁ ንጉስ ነገስት በዳኝነት በሚቀመጥበት ጊዜ ፍትሐ ነገስቱን የሚተረጉሙ፡ በዳኝነት ጊዜም ከንጉስ ግራና ቀኝ የሚቀመጡ እንዲሁም በጠበቃነት ለተሟጋቾች የሚቆሙ ነበሩ። እንዲሁም "ነገስታቱ ሲነግሱ... ስዩመ እግዚአብሔር" ብለው በአክሱም ፅዮን ቤተ ክርስቲያን ቀብተው የሚያነግሱ ታላቅ ከበሬታ ያላቸው ባለሃብት ነበሩ። የማዕከላዊ መንግሥት እየተዳከመ በመጣበት ጊዜ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሊቃውንት በውስጣቸው አንዳንድ የአሳብና የፍልስፍና ልዮነቶች ማለት ቀኖናን አስመልክቶ (doctrine) የተከስተው ተዋህዶ፡ ቅባትና ፀጋ በሚል ክፍፍል ነበር። በዘመነ መሳፍንት ቀሳውስት አንዱ ሌላውን እንደራሴ፡ ባላባትና ባለሌላ ማዕረጎችን በመደገፍ ቤተ ክርስቲያን የበኩሏን አሉታዊ አስተዋፆ አድርጋለች። የመሳፍንቱን ድጋፍ ለማግኘት ህልም/ራዕይ አይተናል "ትንግርት አለህ" ትነግሳለህ እንድንረዳህ የእኛን መስመር ተከተል እያሉ ከተለያዩ መሳፍንት ጋር ቡድን ፈጥረው በብጥብጡ ተካፋይ ሆነው ነበር። እንደ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በመጽሐፋቸው በገጽ 248 እንደሚገልጡት በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ የተከሰተው ክፍፍል ማለት ተዋሕዶ፡ ቅባትና ፀጋ ነበሩ። ዝርዝር ትርጓሜአቸውን ለማወቅ ለምትፈልጉ በዋቢዎቻችን ገጽ ላይ የስፈረውን ይመልከቱ።

<u>*የዘመናዊ ኢትዮጵያ አገር ግንባታ*</u>

በዓለም ላይ የአገሮች ግንባታ በታሪክ ሂደት ውስጥ እንዴት ተመስረተ፡ የሚለውን ስንመረምር አገሮች እንደ አገር ለመሆን የቻሉት እንደአሁኑ ጊዜ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባልነበረበት ሁኔታ ነበር። በአውሮፓ ለምሳሌ ፈረንሳይ፡ ኢጣሊያ፡ ጀርመንና የተቀሩት በአለም ላይ የሚገኙ አገሮችን የአገር ግንባታቸውን ያከናወኑት በጉልበት የተሻለ የጦር መሳሪያ ያለው ወገን በደካማው ላይ የበላይነትን በመጫን ነበር። የዘመናዊ ኢትዮጵያ የአገር ግንባታ ወይም ከዘመነ መሳፍንት በፊት ወደነበረው ሥርዓት ለመመለስ የተደረገው ጥረት ከሌሎች አገሮች የግንባታ ሂደት የተለየ አልነበርም። ለምሳሌ ጀርመንና ህንድ የዘመነ መሳፍንት ሥርዓት ውስጥ አልፈዋል። ኢትዮጵያን ከዘመነ መሳፍንት አላቀው ወደ ማዕከላዊ እራስ አገዝ አስተዳደር እንዲለወጥ ያደረጉት መሪዎች ቴዎድሮስ፡ ዮሐንስና ምኒልክ ናቸው።

አፄ ቴዎድሮስ የጨለማውን የዘመን መሳፍንት በቁጥጥር ስር አውለው የማዕከላዊ ፌደራል መንግስት ማለት ንጉስ ነገስት መንግስት ለማቋቋም የታገሉ ናቸው። የዘመናዊ ተክኖሎጅን በተለይ የጦር መሳሪያ ቴክኖሎጂ እንደመድፍ መስራት የሚችሉ አዋቂዎችን ወደ አገራችን ለማስገባት ያደረጉት ጥረትና ተጋድሎ የሚደነቅ ነው። ዋናው ምኞታቸው የነበረው የማዕከላዊ ፌደራል መንግሥት ተጠናክሮ ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ታላቅነቷ እንድትመለስ ነበር። የአገሪቱም ብሂራዊ ቋንቋ ግዕዝ መሆኑ ቀርቶ አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረውና የሚረዳውን አማርኛ እንዲሆን ማለት የቤተ መንግስቱና የዳኝነትና የስነ ጽሁፍ መገልገያ እንዲሆን አደረጉ።

ኢትዮጵያን ታላቅ የማድረግ ምኞታቸውን እውን ለማድረግ በሚጥሩበት ጊዜ ከቤተ ክህነት፡ ከመሳፍንቱና ከባላባቶች እንዲሁም ከጦር አለቆች በአጠቃላይ ጥቅማቸው ይነካብናል ብለው ከፈሩት ሁሉ ተቃውሞ ደርሶባቸው ነበር። ወታደሩ በደሞዝ እንዲተዳደርና በአርሶ አደሩ ላይ የሚያደርስውን በደልና ብዝበዛ እንዲቆም በመሞከራቸው ቂም ይዞባቸው ነበር። መሳፍንቱም እንደ ዘመነ መሳፍንት ጊዜ ያላስፈላጊ የእርስበርስ ግጭቶቻውን እንዲቆምና ሁሉም በንጉስ ነገሥቱ አስተዳደር ስር መሆን እንዳለባቸው በመወሰኑ ደስተኛ አልነበሩም። የጦር መሪያቸውም ገብርዬ ከደሃ ቤተስብና ከጭቁን ብሂረስብ ከቅማንት የሚወለደውን በማድረጋቸው በመሳፍንቱና በባላባቶች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። የቤተ ክርስቲያን ስዎች እንደአለፈው የዘመነ

መሳፍንት ጊዜ መከፋፈልን ማለት ቅባት፡ ጸጋና ተዋህዶ ማለትን አቁመው በአንድ ቤተ ክርስቲያን ስር በኮሚቴ እንዲተዳደሩ የሚል አሳብ በማቅረባቸው ቂም ይዘውባቸው ነበር።

ከሁሉም ሁሉ መኳንቱንና ባላባቶችን ያስቆጣው በጋፋት የዕደ ጥበብ ፋብሪካ
ባለሙያዎችን አስባስበው ማለት ቀጥቃጮችንና ሸክላ ሰሪዎችን ወዘተ… በአክብሮት ደሞዝ ቆርጠውላቸው በመሳሪያ ማምረት በተለይ መድፍ መስራቱ ላይ እንዲሰማሩ ማድረጋቸው ነበር። በመጨረሻም ለእንግሊዝ መንግሥት የጦር መሳሪያ አዋቂዎች እንዲላክላቸው የጠየቁትን መልስ ባለማግኘታቸው በኢትዮጵያ የሚገኙትን የእንግሊዝ ዜጎች ሰብስበው አሰሩ። የእንግሊዝ መንግሥትም ዜጎቹን ለማስፈታት ወደ መቅደላ ሠራዊት ላከ። የመጣውንም የእንግሊዝ ጦር ለመግጠም ፈልገው ግራ ቀኙን ዙሪያውን ቢመለከቱ ማንም ከጎናቸው አብሮአቸው የቆመ አለመኖሩንና ሲገነዘቡ ለጠላት እጄን አልሰጥም ብለው እራሳቸውን አጠፉ።

አፄ ዮሐንስ የቴዎድሮስን እራይ እውን ለማድረግ ቢጥሩም አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያጠፉት ዳር ድንበሮችን በማስከበርና ወራሪዎችን በመከላከል ነበር። በጀግናው የጦር መሪያቸው አሉላ አባ ነጋ አማካኝነት በምስራቅ በኩል ወራሪ ሀይሎችን ቱርክ፡ ግብፅና ኢጣሊያን ድባቅ መምታታቸውና ከቀይ ባህር ማባረራቸው እንዲሁም የአስመራ ከተማን በመቆርቆራቸው ይበልጥ ይታወቃሉ። በመጨረሻም በራሳቸው በአፄ ዮሐንስ በጦር አዝማችነት የጎንደር ከተማ በደርብሾች (ሱዳኖች) በመቃጠሉና በመዘረፉ፡ ወራሪውን ጦር እስከ መድኔ ገዳሪፍን አልፎ እያባረሩ እያሉ በአጋጣሚ በሱዳኖች በተተኮስ ተባራሪ ጥይት ተመተው ስለሞቱ፡ የሱዳን ወታደሮች አንገታቸውን ቆርጠው በሱዳን ከተሞች እንዲዞር አደረጉ። የተቆረጠው ጭንቅላታቸው እስከ አሁን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በክብር መቀበር ሲገባው በሱዳን ሚዝየም ውስጥ ይገኛል።

አፄ ምኒልክ የቴዎድሮስንና ዮሐንስን ራዕይ በተግባር የተረጎሙ ታላቅ መሪ ናቸው። ከሁለቱ ንጉስ ነገስቶች የተቀበሉትን የማዕከላዊ ፌደራል መንግስት አስተዳደር እንዳለ ተቀብለው ቀጥለውበታል። በአድዋ የዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀውን የጣሊያንን ጦርን ድል በማድረግ የጥቁር ሕዝብን ያኮሩና የነጩን ሕዝብ ያሳፈሩ ናቸው። በጦርነቱም መላውን

ብሄረስቦች በኢትዮጵያዊነት ለማሳተፍ የቻሉ ጀግና አስተዋይ መሪ ናቸው። አፄ ምኒልክ ከአድዋ በድል አድራጊነት ወደ መናገሻቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ለዘማቹ ስራዊት በወሮታ መልክ በደቡብ ኢትዮጵያ ባልዘመተው ሕዝብ ላይ መሬት መሩበት። እኛ እስከምናውቀው ድረስ ይህ በዘመናዊ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው የጢሰኛና የባለመሬት ስሪት ታሪካችን ነው። የተመሩት ሠራዊት አባሎች ከተለያዩ ብሄረስቦች በአብዛኛው ከሸዋ፣ ከጎንደር፣ ከጎጃምና ከትግሬና ከኦሮሞ የመጡ ነፍጠኞች (ጠመንጃ ያገሮች) ነበሩ።

በአለም ላይ ከሚገኙት የዘመናቸው መሪዎች መካከል አፄ ምኒልክ አስተዋይና የዲፕሎማሲ ሰው እንዲሁም ሩህሩህና ይቅር ባይ መሪ እንደነበሩ ብዙዎች ይመስክራሉ። በተቻለ መጠን ችግሮችን ከጦርነት ይልቅ በስላም ለመፍታት
ይመርጣሉ። ብልሂቱ ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ አዲስ አበባ ከተማን የቆረቆሩት ከቤተ መንግስት አስተዳደርና ዲፕሎማሲ እስከ አድዋ ጦርነት በግንባር በመሳተፍ ለኢትዮጵያ ሴቶች አርአያ የሆኑ ጀግና ሴት ናቸው። አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ዘመናዊ የዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት፣ የባቡር መስመር ከጂቡቲ አንስቶ በድሬ ደዋ አቋርጦ አዲስ አበባ የሚደርስ፣ የፖስታና የቴሌግራፍ አገልግሎት እንዲሁም የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ለማቋቋም የበቁ ታላቅ መሪ ነበሩ። አስተዳደራቸውም የፌደራል ማዕከላዊ ንጉስ ነገሥት ነበር። በተቻለም መጠን ሁሉንም በእኩል አይን ለማየትና ለማሳተፍ የጣሩ ንጉስ ነበሩ።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የፌደራላዊ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲፈርስና አህዳዊ ፍጽም ማዕከላዊ መንግስት ማለት እራስ አገዛዝ ክፍሎች ወደ ጠቅላይ ግዛትነት እንዲቀየሩ የተደረገበት ነው። ለዚህም ለውጥ ስኬታማነት የዘመናዊ ጦር ሠራዊትና ቴክኖሎጂን ማለት አውራ ጎዳንን፣ አውሮፐላንና የስልክና የቴሌግራፍ መገናኛዎችን በሚገባ ተጠቅመውበታል።

በመንግስትና በሃይማኖት መካከል የነበረውን ግንኙነት ለመገደብ "አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው" የሚለውን መርሆ ለመጠቀም ሙከራ ተደርጓል። የድሮውን ዓይነት ግንኙነት ማለት ፍትሃ ነገስት በዘመናዊ ሕገ መንግሥት እንዲተካ ተደርጓል። ሕገ መንግስቱ ዘመናዊ ስንል በቅርጽ እንጂ በይዘት ፍጹም ማዕከላዊ የሆነ ሁሉም ነገር በንጉሱ

መልካም ፈቃድ የሚደረግ ነበር። ንጉሱም የእዮቤል በዓላቸውን ሲያከበሩ ሕገ መንግስቱ ተሻሽሎ እንዲወጣና ፓርላማ እንዲቋቋም ማለት የመወስኛ ምክር ቤት በንጉሱ የሚሾሙና የሕዝብ ምክር ቤት በሕዝብ የሚመረጥ እንዲሆን ፈቅደው ነበር። ፓርላውም የተሞላው በባለመሬቶችና በመኳንት ስለነበር ጥቅማቸውን የሚጻረር ውሳኔ አያሳልፉም ነበር። የፓርላማው ውሳኔዎች ምንም ይሁን ምን በሥራ የሚውሉት የንጉሱ መልካም ፍቃድ ሲያገኝ ብቻ ነበር።

በንጉሱ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የመከላከያ ስራዊት በዘመናዊ መልክ ማለት ወታደሩ በደሞዝ የሚተዳደር ሆኖ ተቋቋመ። የመከላከያ ተቋሞች የሆለታ ጦር ት/ቤት፣ የሐረር አካዳሚ፣ የፖሊስ አባዲና፣ የአየር ሃይል አካድሚና የባሕር ሃይል ኮሎጅ ለማቋቋም ተችሎ ነበር። የመከላከያ ሠራዊትም የክብር ዘብኛ፣ የጦር ስራዊት፣ የፖሊስ ስራዊት፣ የአየር ሃይል፣ የባህር ሃይል በኋላ ሚሊሻን አባሎችን ያጠቃለለ ነበር።

የንጉሱ አስተዳደር አድልዖና የአስተዳደር ብልሹነት የተጠናወተው ቢሆንም በንጉሱ ዙሪያ የነበሩ አንዳንድ ሹማምንት በውጭ ጉዳይ የተጫወቱት የዲፕሎማሲያዊ ስራዎች የሚናቁ አልነበሩም። ለአብነት ከእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር እንዴት በዘዴ ለማምለጥ እንደተቻለና ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል
መደረጉ ናቸው። ብዙ የዚያን ዘመን የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚስማሙበት ንጉሱ አንድ ያመለጣቸው እድል ዓለምን ዞረው ከነበኙና የተለያዩ አገሮችን የአስተዳደርና የእድገት ክንዋኔዎችን ከአዩ በኋላ ጠቅላይ ግዛቶችን አጥፈው ወደ ቀድሞው የእራስ አገዛዞች ማለት አንዳንድ ማሻሻያዎች በማድረግ ለመቀየር ሲችሉ አለማድረጋቸው ነው። ማለት እንደ እንግሊዝ ዓይነት አሃዳዊ ፌደራል አስተዳደር ማለትም በሕገ መንግስት (constitutional monarchy) የሚገዛ መንግሥት ማድረግ ይችሉ ነበር። ይህን አድርገው ቢሆን ኖሮ ከአጓጉል አወዳደቅ ይድኑ ነበር ብለው የሚወቅሱዋቸው ጥቂቶች አይደሉም። ንጉሱ በለውጥ ፈላጊና በወግ አጥባቂ መካከል የተወጠሩ ነበር ማለት በመጨረሻው ወደ ወግ አጥባቂው አዘንብለው ነበር ማለት ይቻላል። ሌላው ጣጣ የኤርትራ ጉዳይ ነው። የነበረውን ፌደሬሽን ፈርሶ ወደ ጠቅላይ ግዛትነት መለወጡ እራሱን የቻለ ችግር በአገራችን ላይ ፈጠረ። በዚህ ስህተታችን የአገራችን ታሪካዊ ጠላቶች በመጠቀም የነፃ አውጪ ድርጅቶችን ሙሉ ድጋፍ በመስጠት አገራችን

እንድትዳከምና ወደቀድሞው ዘመነ መሳፍንት እንድትመለስ ያላሰለሰ ጥረታቸውን እንዲቀጥሉ አበረታቶአቸዋል። እንግዲህ አንባብያን በተለይም ወጣቱ ትውልድ ልብ እንድትሉልን የምንፈልገው ቁም ነገር የኢትዮጵያ ተማሪዎች በመንግስት ላይ ተቃውሞ ማስማት የጀመሩበት በዚህ ወቅት መሆኑ ነው። አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ተማሪዎች ጠግበው እንዲሁም ለምን የልማት ሥራዎች ተሰሩ ማለት ት/ቤቶች፡ ሆስፒታሎችና ፋብሪካዎች ሳይሆን ሕዝብ ተበደለ፡ ፍትሕ ተጓደለ እንዲሁም እድገታችን ከአዲሶቹ ነፃነታቸውን ካገኙ የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲወዳደር እድገታችን አዝጋሚ ሆነ በሚል ቅዱስ ቅናት እንደነበረ እንድትገነዘቡልን እንፈልጋለን።

## የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል የጀመሩት በአገራችን ምንም ዓይነት የፖለቲካ ድርጅት በሌለበት ወቅት ነበር። ለትግላቸው መነሻ የሆነው በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ በመገንዘብ “መሬት ለአራሹ” የሚለውን መፈክር አንግቦ ነበር። በ60ዎቹ መጀመሪያ ባለመሬቶች በትራክተር ለማረስ ሲሉ ጭሰኛ ገበሬዎችን ከአለሙት መሬት እንዲፈናቀሉና ወደ ጭንጫ ያለማ መሬት እንዲዛወሩ በመደረጉ በጭሰኞችና በባለመሬቶች መካከል የነበረው ቅራኔው ተስፋፍቶና ተካሮ በነበረበት ወቅት ነበር።

በደቡብ ኢትዮጳያ የብሄረሰብ ጥያቄ ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነበር። በስሜን ኢትዮጵያ የነበረው የመሬት ይዞታ ከደቡቡ በጣም የተለየ ነበር። በስሜን የነበረው ርስተ ጉልት ማለት የአካባቢው ተውላጅ በሙሉ መሬት ይነስ ይብዛ እንጂ የግንባር ቆዳ የምታክልም ቢሆን የማግኘት ሕጋዊ መብት ነበረው። ከመንግስት ጋር የነበራቸው ችግር ግብር መጨመርና መቀነስ እንዲሁም የልማት ሥራዎችና ትምህርት ቤትና ሆስፒታል ወዘተ…የመሳሰሉት አልተሰሩልንም ነበር። እዚህ ላይ ለአሁኑ ወጣት ትውልድ የምንመክረው እራሳቸውን ከአስመሳይና አወናባጅ ድርጅቶች እንዲጠብቁ ነው። አገራችን ያለችበት ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ነው። የወቅቱ ጥያቄ ህልውናችንን ማስጠበቅና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ነው። በትግሉ ይበልጥ ለመሳተፍ ከእኛ ጊዜ የተሻለ ተመክሮዎች ያላቸው ሀቀኛ የፓለቲካ ድርጅቶች እንደ ኢሕአፓ የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነው። ስለዚህ ትግላችሁን ከሀቀኞች ጋር አስተባብሩ እንላለን። በቅድመ አብዮት

የነበረውን የመሬት ይዞታንና ስሪት በተመለከተ የደሳለኝ ራህመቶ ሥራዎችን ማለት ምርምሮችን ከቤተ መጻሕፍት ፈልጋቸሁ እንድታነቡ እንናሳስባለን።

የቅድመ አብዮት የኢትዮጵያን ከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት ሥርዓት በሙሉ እንዘርዝር ከተባለ በጣም የሚንዛዛ ስለሚሆንብን ከርዕሳችን ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባላቸው ላይ ብቻ ትኩረት ለመስጠት ተገደናል። እዚህ ላይ በእድሜአችን ያየነውን በእርግጠኝነት መመስከር የምንችለው ቁም ነገር በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሄረስቦች የተበደሉ መሆናቸውን ነው። የበደሉ ዓይነትና መጠን ይብዛና ይቀንስ እንጂ ሁሉ የስርዓቱ ስለባ ነበሩ። እንደ እውነቱ ከሆነ ነገር የተበላሸው በአፄ ሃይለ ሥላሴ ዘመን የንጉስ ነገስት ፌደራላዊ ሥርዓት ተሰርዞ ወደ ክፍላተ አገር በመቀየሩ ነው። ለምሳሌ ወሎ፣ ጎጃምና ጎንደር እንዲሁም የቀሩት ክፍላተ አገሮች የራሳቸው አካባቢ ተወላጆች በአስተዳዳሪነት ተሹሞላቸው ያውቅም ነበር፤ ትግራይ ቢያንስ የራሱ ተወላጅ የሆነ አስተዳዳሪ ነበረው። በአጠቃላይ የክፍለተ አገር ማህበራዊ አገልግሎትና ስርጭት ከጥቂቶች በስተቀር አጥጋቢና ፍትሃዊ አልነበረም። ለምሳሌ ደብረ ማርቆስ የጎጃም ዋና ከተማ ወደ ባህር ዳር ከመቀየሩ በፊት ደብረ ማርቆስ ከተማ የኤሌትሪክ አገልግሎት አልነበረውም፣ የሚገለገለው በማሾ/ፋኖስ ነበር፣ የከተማው አውራ ጎዳና አስፋልት ሳይሆን አቧራ መንገድ ነበር። በሸዋም እንደመንዝ የመሳሰሉት አካባቢዎች የሕዝቡ ኑሮና ማህበራዊ አገልግሎች ከሌሎች የተጨቆኑ ብሄረስቦች ጋር ተመሳሳይ እንደውም ያነስ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ስለዚህ የአማራን ሕዝብና የገዢውን መደብ በደፈናው ሁሉንም ጨቋኝ አድርጎ ማቅረቡ ስህተት ነው። እንዲህ ያለ አባባል በእኛ ግምት ምንጩ ጭፍን ጥላቻ አልያም የመደብ ትንተናን አለማውቅ (የሁለቱም ድብልቅ) ነው። በበኩላችን የወያኔ መሪዎችና አጫፋሪዎቻቸውን ከትግራይ ሕዝብ ጋር ደምረን በአንድ ዓይን/መነጽር አናያቸውም። ወያኔዎችና እነሆድ አምላኮች የትግራይን ሕዝብ እንደተጠቀመ አስመስሎ በማቅረብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማጣላትና ለማለያየት የማይፈነቁት ድንጋይ እንደማይኖር ብዙዎቻችን የምናውቀው ጉዳይ ነው።

መቼም ነገርን ነገር ያመጣዋልና ይህን ጽሁፍ በምናዘጋጅበት ጊዜ ለኢትዮጵያዊ ስማይ (Ethiopian Semay blogs) አዘጋጅ ከአንድ

ፕሮፌሰር የተላከ "ደብዳቤ አይሉት" ወይም "ቀጭን ትዕዛዝ" ተመልክተናል። የጽሁፉም ይዘት እንጋፋውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች አባል የነበረውን ዋለልኝ መኰንን ስለብሄር ጥያቄ የአራተኛ አመት ተማሪ እያለ በታገል መጽሔት (vol.5, No.2, November 17, 1969) የጻፈውን አስመልክቶ ነው። እዚህ ላይ ለአንባቢያን ግልጽ ማድረግ የምንፈልገው ከፕሮፌሰሩ ጋር እስጥ አገባ ለመግጠምና የመተቸት መብታቸውን ለመገደብ አለመሆኑ ይታወቅልን። ሆኖም ዋለልኝ እራሱን ለመከላከል (defend) በሕይወት ስለሌለ እንዲሁም ወጣቱን ትውልድ ከውዥንብር ነፃ ለማድረግ አስፈላጊ ነው ብለን ስለአመንበት በዚህ ጉዳይ አንዳንድ የምንለው አለን። የዋለልኝ ጽሁፍ በጊዜው የተራማጅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ነፀብራቅ ነበር ማለት በጊዜው ሁላችንም የምንጋራው አስተሳሰብ ነበር። ነፍሱን ይማረውና በሕይወት ቆይቶ ቢሆን ኖሮ እሱም እንደ እኛ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርምር መገንጠል የመፍትሔ አሳብ ሊሆን እንደማይችል ተገንዝቦ አቋሙን ያስተካክል ነበር። ሌላው የሚያሳዝነው ጉዳይ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ያውም የአራተኛ አመት እንዲህ ያለ ጽሁፍ እራሱን ችሎ መጻፍ አይችልም መባሉ ነው። ተማሪ ዋለልኝ መኮንን የሲ.አይ.ኤ ቅጥረኛ አልነበረም። በእርግጥ ማርክሲስትና ከዚያም አልፎ የህብረተሰብ/ሴሲኦሎጅ ተማሪ ነበር። በመሆኑም ምርምር የማድረግ እድሉ ሰፊ ነበር።

የዘመናዊ ሥልጡን ወቃሾች በዚያን ዘመን የፌውዳሉ ሥርዓት አቀንቃኞች የነበሩ ማለት በኢትዮጵያ የመደብ፡ የሃይማኖትና የብሄረሰብ ጭቆናና በደል አልነበረም ባዮች የነበሩ ናቸው። የግራ ዝንባሌ የነበራቸው ተራማጅ ተማሪዎች ደግሞ ሕዝባችን ተበድሏል፡ ፍትሕ ተጓደለ እድገታችን አዝጋሚ ሆነ እንዲሁም በገበሬው በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚደርስበትን ግፍ ለማቆም "መሬት ለአራሹ" ብለው፡ በኋላም በኢ.ሕአፓ መሪነት በደርግ ዘመን ዴሞክራሲ ያለገደብና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ወዘተ መፈክሮች ስር ታግሏል ሕዝባችንንም አታግሏል።

አሁን ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነና ታዲያ "ላም ባልዋለበት ኩብት ለቀማ" ሆኖ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጣታቸውን በኢ.ህአፓ ላይ መቀስርና በሀሰት መክሰስ ሥራችን ብለው ተያይዘውታል። በተለይ በአሁኑ ወቅት አገራችን በአደጋ ውስጥ በምትገኝበት ጊዜ በእንደዚህ ያለ ፋይዳቢስ ነገር ከመጠመድ ይልቅ ፓርቲው በሂደት አስተካክሎ

የደረስበትን አቋሙን በልሳኑ በዴሞክራሲያ በግንቦት 1994 ያወጣውን ልዩ እትም "ኢህአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ" ቢያነቡና ባለማወቅ ከሆነም የሚፈጸሙት ውኽ'ንብር ከመንዛት ተግባራቸው ታቅበው፤ ለጥፋታቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ አገር ማዳኑና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ መሳተፉ ይበጃቸዋል ብለን እንመክራለን። ከዚህ ውጭ "በሬ ወለደ" ማለቱ በአውቆ አጥፊነት የሚያስፈረጅና ወደፊትም በትውልድና በታሪክ በወንጀለኛነት፥ በአድርባይነትና በቅጥረኛነት የሚያስጠይቅ ነው እንላለን።

በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰቦች ላይ ይደርስ የነበረውን በደልና ጭቆና አሁንም በከፋ መልኩ ቀጥሎ የሚገኘውን ለማወቅ ለምትፈልጉ ሁሉ ከእኛ እይታ ያልተበረዘና ያልተከለሰ ታሪኩን በአጭሩ እናውጋችሁ። በአሁኑ ወቅት የወያኔ አምባገነን መንግሥት የብሄረሰቦችን ሰብአዊ መብት ረግጦና የዴሞክራሲያዊ መብት ነፍጎ ሁሉን አድራጊና ፈጣሪ በመሆን ብሄረሰቦችን የሚያስተዳድራቸው በሞግዚትነት ልክ እንደዘመነ መሳፍንት አባወራ በመሆን ነው። በካድሬዎቹም አማካኝነት በሆነውና ባልሆነው ጥቃቅን ጉዳዮች ለምሳሌ በድንበር ይገባኛልና የሃይማኖት ግጭቶችን እየቀሰቀ አንዱን የደገፈ ሌላውን የተቃወመ በመምሰል ሕዝባችንን እያጫረስ ይገኛል። ክልሎች ከባንዲራ በቀር ያገኙት ምንም ትርፍ ነገር የለም። የወያኔ ፌደራል አወቃቀሩ በብዙ መልኩና የይዘቱ ከቀድሞ የሶቪየት ህብረት ጋር በጣም ይመሳሰላል። ማለት ፍጹም ማዕከላዊ አምባገነን ሥርዓት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥም የክልል ተወካዮች ተብዬዎችም "በሕገ መንግስት" ተሰጣቸው በተባለውን መብት የመጠየቅ ወኔውም የላቸው። የተባለው መብት በወረቀት ላይ ከመስፈሩ በስተቀር በስራ ላይ እንዳይውል ወያኔ እራሱ ላወጣው ሕግ ተገዢ አይደለም። ስለሆነም ክልሎች ሌላው ቢቀር የሚያስፈልጋቸውን የአመት ባጀት እንኳን ማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ናቸው። ወያኔ የኦጋዴንና፥ የደቡብ ሕዝባችን በሰው ሰራሽ ርሃብና የዋጋ መናር እንዲሁም በኑሮ ውድነት እየቀጣቸው ነው። እንዲሁም በማያገባው በሰው አገር ውስጥ ገብቶ ማለት በሱማሊያ ውስጥ በጦርነት እየዳከረ ማጣፊያው ጠፍቶበት እየተደናበረ ይገኛል። የሚያሳዝነው በማያገባው ገብቶ ጭቁን ወታደሮችን በከንቱ እንዲያልቁ መደረጉ ነው።

በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ችግር የነበረና አብሮን የኖረ ነው። ተማሪው የፈጠረው አዲስ ክስተት አይደለም። በመሰረቱ ጭቆና ብዝበዛ ባሉበት ሥርዓቶችን ሁሉ ተጨቋኙ ወገን ተደራጅተውም ሆነ በግብታዊነት

መቃውም ወይም ማመፅ ያለነገር ነው። በኢትዮጵያም አመፅ የተጀመረው በእኛ ዘመን ተማሪዎች የነበርን አብዛኞዎቻችን ከመወለዳችን በፊት ወይም ህጻን በነበርን ጊዜ ነው። በአገራችን የብሄረስብ ችግሮችና ተቃውሞዎች ማለት አመፆች የተነሱት ቀደም ሲል ነበር፡፡ ለአብነት ለመጠቃቀስ ያህል በ1940ዎቹ የትግራይ አርሶአደሮች አመፅ፡ በ1950ዎቹ የኦሮሞ እንቅስቃሴ በሜጫ ቱለማ የመረዳጃ ድርጅት ተጀምሮ በኋላ በባሌ የእነዋቆ አመፅ፡ ከዚያም የጎጃም አርሶአደሮች የብቸና የግብር መጨመርን በመቃውም የተነሳው አመፅ በመጨረሻም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የነበረው ፌዴሬሽን እንዲፈርስ በመደረጉ የጀብሃ እንቅስቃሴ ተጀምረው ነበር። ታዲያ ይህን የተገነዘበ የኢትዮጵያ ተማሪ ማህበር ለሕዝባችንና ለአገራችን ባለው ቀንአዊ ፍቅር የበለጠ አንድነትና እድገት ለማምጣት የብሄረስብ ችግሮችን ለመፍታት በጊዜው በነበረው የእውቀት ደረጃና ግንዛቤ ተመርኩዞ "ብሄር ብሄረስብ የራሱን እድል በራሱ የመወስንና እስከ መገንጠል" ያለውን መብት እንደመፍትሔ አሳብ አድርጎ አቅርቦ ነበር። በትግል ውስጥም በመሳተፍ ባገኘነው ተመክሮ ጉዳዩን ስናየው "እስከ መገንጠል" የሚለው ትክክልና በሥራ ላይ ለማዋል የማይቻል ንድፈ አሳብ መሆኑ ለመገንዘብ የቻልንበት ደረጃ ደርስናል። አሁንም የትግል መርሆአችን በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄረስቦችን የራስን እድል በራስ የመወስን መብት ማክበርና እኩልነታችን በማስረገጥ የሁላችን የምትሆን ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሪፓብሊክ መመስረት ነው።

የአገራችን የቆዳ ስፋት እንደ ዘመኑ ሁኔታ ሲተልቅና ሲቀንስ አሁን ያለንበት ወቅት ደርስናል። አገራችን ለሁላችንም የሚበቃ የተፈጥሮ ሀብት ማለት ለእርሻ ተስማሚ ለም መሬት፡ ማዕደናት፡ ወንዞችና ሐይቆች እንዲሁም ታታሪ ሕዝብ አለን። የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በትግላችን ከመስረትን ፍትሃዊና ማህበረስባዊ የገበያ ኤኮኖሚ መገንባቱ ያን ያህል አይከብድም። እንደ ጨው በዓለም ተበትኖ የሚገኘውን የስለጠነ የስው ሃይል አስባስቦ ልማትና እድገት ማምጣት ይቻላል። የህብረተሰባችን አንድነትና ልዩነትን አስመልክቶ የኢሕአፓ ልሳን ዴሞክራሲያ. የግንቦት 1994 ልዩ እትም እንደሚከተለው ያብራራል፡

*የኦሮሞው፡ የወላይታው የጉምዙ፡ የሀዲያው፡ የአማራው፡ የትግሬው ወዘተ...ሕዝብ የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ባለቤት ነው እንጂ ኢትዮጵያዊነቱን ለማስረገጥ ድርድርን አይፈልግም። ይህንን የሚክዱ*

ናቸው በሕዝብ አንድነት ላይ መርዝ የሚረጩ ማለትም ይቻላል። በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ገደብ ሊጥሉብን ግድፊት ሲፈጥሩብን ሊያውገረግሩብንና ማንነታችን ሊክዱ የተነሱ ሥርዓቶች የምንታገላቸውም ከዚሁ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ካለን ጠንካራ ዕምነት የተነሳ ነው። ኢትዮጵያዊነታችንን ሲክዱ አዎን ብለን መቀበል ሆነ መገንጠልን ማቀንቀን ደግሞ ስህተት መሆኑም ሊታመንበት ይገባል። በመሆኑም ኢሕአፓ ለመብታቸው ከሚታገሉት ጎን እየቆመና እየታገለም ኢትዮጵያዊነትን በመካድ ለሚቀኝ የትግል ምርጫ ወይም ፕሮግራም ግን ተቃውሞውን ያስማል እንጂ ድጋፉን አይሰጥም። ጭቆና ስለተባለ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይዘቱና ሚዛኑ ሳይጋነን መታወቁ የግድ ነው እንላለን፡፤ የወያኔን በሬ ወለደ ዓይነት የታሪክና የህቅ ክለሳ ስንመለከት በጉዳዩ ላይ ይበልጥ ጥንቃቄ እንድናደርግ ሊጋብዘን ይገባል። ማን ይበልጥ ተጨቀነ ማንስ ከዚያ ባነሰ ደረጃ ተበደለ በሚለው አንጉል ክርክር ባንገባም አንዳንድ ጉዳዮችን መጠቆም ግን እንወዳለን። ቢያንስ ትግራይ ለምሳሌ በጪሰኛ ስርዓት አለመበደሉን፡ አድልዎ ተደረገ ከተባለም በአንድዳንድ መስኮች ሁኔታው ወያኔ ጨቋኝ የሚለው ሕዝብ ራሱ ከሚኖርበት ሁኔታ ያልተናነሰ እንደነበረም መጥቀስ እንችላለን። አንፃሩ ደግሞ ኢትዮጵያዊነታቸው በጥያቄ ገብቶ የቆዩ ሕዝባች..አንዳንዶቹ በደርግ ጊዜ ወደ ፖለቲካው ዓለም የተሳቡ...እንደነበሩም እንናያለን።

## ብሄረሰብ ማንነት (Identity)

የብሄረሰቦች ማንነታቸውን ከመግለጻችን በፊት አለም አቀፉዊ የሕዝቦች ፍልስትና ስፈራ

እንቅስቃሴዎች ማለት ተቀባይነትና አመኔታ ያላቸውን ንድፈ አሳቦችን መጥቀስ እንፈልጋለን። ይኸውም የአለም ሕዝቦች በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች በአገራቸው ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ከአንድ ቦታ ሌላ ቦታ በግለስብና በቡድን ያለማቋረጥ ይንቀሳቀሳሉ (migration) እንዲሁም ከአገር ውጭ ወደ ሌላ አገር (immigration) ይፈልሳሉ። በኢትዮጵያም የተለያዩ ብሄረስቦች ከስሜን ወደ ደቡብ፡ ከደቡብ ወደ ስሜን እንዲሁም ከምስራቅ ወደ ም ዕራብ፡ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በፍልስት፡ በስፈራ (migration and settlement) አማካኝነት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰዋል። የእንቅስቃሴው ብዛቱ፡ መጠኑና ምክንያቶቹ ይለያዩ እንጂ እንቅስቃሴው ሁልጊዜም ቀጣይና የማያቋርጥ ሂደት ነው ማለት ይቻላል። ብሄረስቦችን አቀማመጥና ስርጭት በአንዳንድ ክፍላተ አገር

ወይም በአሁኑ ክልል በመስባጠር፡ በኩታ ገጠምተኝነት፡ እንዲሁም ትንንሾቹ በትልልቆቹ ተከበው ይገኛሉ። በመሆኑም አብዛኛው ህብረተሰብ ከአንድ ቋንቋ በላይ ተናጋሪ ነው። አንድ ቁም ነገር መገንዘብ ያለብን እያንዳንዱ ብሄረሰብ ራሱ የሚቀበለውና የሚያምንበት መታወቂያ ወይም መጠሪያ ስም እንዳለው ነው። ከዚያ በተጨማሪ አንዳንድ የውጭ አገር ፀሐፊዎችና አጎራባቾች ብሄረሰቦች አንዱ ለሌላው በሚሰጡት የተለየ ስም ምክንያት የብሄረሰብን ብዛትና ቁጥር በእርግጠኛነት እንዳይታወቅ መስናክል መሆኑን ነው። ለምሳሌ የጉሙዝ ብሔርስብ አባላት ራሳቸውን ቤጋ ወይም ባጋ ብለው የሚጠሩ ሲሆን በሌሎች ብሔርስቦችና ተመራማሪዎች ገንዛ፡ ጓንዞ፡ ጉሚስና ሻንቅላ በሚል ስያሜ ይጠሩታል። በመሆኑም ይህ ብሄረስብ በአራት የተለያዩ ስሞች በመጠራቱ ምክንያት እንደአራት የተለያዩ ብሄረስብ ተደርጎ የመወሰድ አዝማሚያ በመንጸባረቁ የብሄረስቡ ቁጥር በአንዳንድ አካባቢ እንዲጨምርና በሌላው እንዲቀንስ ምክንያት ሆኖአል። በመሆኑም እስከአሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄረስ ጉዳይ በደንብ ቀጣይነት ባለው መልኩ ባለመጠናቱ በእርግጠኝነት ምን ያህል ብሄረስብ እንዳለ ለማወቅ ባይቻልም በደፈናው ከ70 እስከ 80 የሚደርሱ ብሄረስቦች አሉ ተብሎ ይገመታል።

በደርግ ዘመን ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የብሄረስቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የሕዝባችን ፍልስትንና የስፈራውን ዓይነትና፡ መጠን እንዲሁም ምክንያትና ሂደቱን የሚያስረዳ ጽሁፍ (booklet) አዘጋጅቶ ነበር። ጽሁፉም የተዘጋጀው በደርግ መንግስት የበላይ ተቆጣጣሪነት በመሆኑ ከፖለቲካ ተጽእኖ ነፃ ሆኖ የተዘጋጀ ነው ለማለት ባያስደፍርም፤ የብሄረስቦችን ማንነትና የአስፋፈር የሚያስረዳ ጽሁፍ በመሆኑ፤ ለወደፊት ተመራማሪዎች በፍንጭ ሰጭነት ይረዳል የሚል ግምት ስለአለን በብዛት በዋቢነት ተጠቅመንበታል። ጥናቱም የብሄረስቦችን አስፋፈር እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

- *በማናቸውም ጎሳ፡ ብሄረስብ ወይም ብሄር ለዘመናት የኖረበትና የሚኖርበት ሪክ የታወቀ ብሄራዊ ክልል ይኖረዋል። ይህ ዓይነት አስፋፈር "ታሪካዊ፡ ብሔራዊ" አስፋፈር ይባላል። ሁለተኛው ያስፋፈር ዓይነት- ያንድ ጎሳ ወይም ብሔረስብ አባል በጦርነት፡ በችነፈር፡ ወይም በማናቸውም የተፈጥሮ ተፅዕኖ ምክንያት ከዋናው ብሔርስቡ በመነጠልና በታሪክ የታወቀ አካባቢውን በመተው በሌላ አዲስ ቦታ የሚገኝበት ሁኔታ ነው።*

- *ሶስተኛው ያስፋፈር ዓይነት- ያንድ ብሔረሰብ ወይም ብሄርስቦች እና በቡድን ወይም በተናጠል ለምርት፡ ለንግድ፡ ለጋብቻ፡ ለአስተዳደር ወዘተ. ተግባር ከብሄርስባቸው ተነጥለው በመሄድ በሌላ አካባቢ ከሌላ ብሄረሰብ ኅብረተሰብ ጋር በመቀላቀል የሚኖርበት ሁኔታ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ አስፋፈር "ማህበራዊ ስርጭት" ሊባል ይችላል።*

የእኛ ጥናት ዋናው ትኩረትና ተስፋችን ወጣቱ ትውልድ የብሄረስቦችን አንድነትና ልዩነት፡ ማንነት፡ እንዲሁም አኗኗራቸውን፡ ቋንቋቸውን፡ ባህላቸውን፡ ችግራቸውንና ብሶቶቻቸውን በሚገባ አውቆ፡ በመፍትሔ ፍለጋው ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ነው። ለዚህ ተግባር ወጣቱ ትውልድ ጉዳዩን ይበልጥ እንዲረዳው በማስብ ከትልልቆቹ፡ ከመካከለኛዎቹና ከትንንሽዎቹ ማለት የተረሱ ብሄረስቦችን መካከል ጥቂቶቹን ለናሙና ያህል ዘርዘር አድርገን እናቀርባለን።

## <u>*ትልልቅ ብሄረስቦች*</u>

### <u>*ሀ. የኦሮሞ ሕዝብ*</u>

የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ብሄረስቦች አንዱ ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ75 እስከ 80 ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ይገመታል። ሆኖም አሁን በወያኔ የሚደረገው ወይም የተደረገው የሕዝብ ቆጠራ (data) የፓለቲካ እንደምታ ያለውና የፈለገውን በመጨመርና በመቀነስ አስተማማኝ ባለመሆኑ ከስላሳ አመት በፊት የተደረገውን የሕዝብ ቆጠራ መረጃ (central Statistical Office, data 1978) መጠቀሙን መርጠናል። ያም ሆኖ በማንኛውም መለኪያ የኦሮሞ ሕዝብ ብዛት ከፍተኛ መሆኑ ክርክር ውስጥ የሚገባ አይደለም። በደርግ ዘመን ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ብሄረሰብ ኢንስቲትዩት ጥናት የኦሮሞ ሕዝብን አስመልክቶ እንዲህ ይላል።

*በኦሮምኛ ቋንቋ "ኢልማን ኦሮሞ፡ አፋን ኦሮሞ፡ ቢያ ኦሮሞ" የሚለውን አነጋገር በቅደም ተከተል ሲተረጎም የኦሮሞ ልጆች፡ የኦሮሞ ቋንቋና የኦሮሞ አገር ማለት ይሆናል። የኦሮሞ ዘመድ ብድኖች ሁሉ በእነዚህ ሶስት ስንኞች ውስጥ በሚገኘው ኦሮሞ በሚለው ቃል ምትክ ሌላ ተለዋጭ ቃል አይጠቀሙም ሁሉም ኦሮሞ በሚለው ቃል ይስማማሉ። ... የኦሮሞ ብሄረሰብ በስሜን ምዕራብ ከጉሙዝና ከሺናሻ፡ በስሜን*

*ከአማራ፥ በስሜን ምስራቅ ከአፋር፥ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ከሶማሊ፥*

*በማህል ደቡብ ከአላባ፥ ከጉራጌ፥ ከቀቤና፥ በማህል ምዕራብ ከየምሣ፥ ከዳውሮ፥ ከከፋ፥ ከሞቻና ከመስንጎ፥ በምዕራብ ከአኙዋክ፥ ከኑዌር፥ ከማኦ፥ ከኮሞ፥ ከጀብላዊ በድምሩ ከሀያ ስድስት በላይ የተለያዩ ብሄረስቦች ሲጎራብት ከአንድ የውጭ አገር (ኬንያ) ጋር ይዋሰናል።*

በተለያዩ አካባቢዎች የኦሮሞ ሰዎች በራሳቸውና በአጎራባች ብሄረቦች የሚጠሩበት ስሞች አላቸው። ይኸውም ግጂ/ጀምጀም፥ አላብዱ፥ ታትራት፥ ኦላ፥ ጃንጃማ፥ ኡራጌ/አርሲ፥ ቦረና/ጌርጌዳ፥ ራያ፥ ሜጫ፥ ቱለማ፥ ቆቱ፥ ገሪ፥ ግብራ፥ ወረዱቤ፥ ከረዩ፥ ዱቤ፥ አብቼ፥ በቾ፥ ሊቃ፥ ገላን፥ ስላሌና ጂሌ እያሉ ራሳቸውን በተለያዩ በትውልድ አገሮቻቸው ስም ይጠራሉ፡፡ በኦሮሞ ውስጥ አንድ ወጥ የሆነ ማለት ኦሮምኛ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን ብዙ ብሄረቦች ተደባልቀው፥ ተስባጥረውና በመከበብ ታቅፈው ይገኛሉ፥ እንደ የብሄረቦች ኢንስቲትዩት 1978 ዓ.ም ገለጻ፤

*ብሄረስቡ በያዘው ስፍራ ተስባጥረው የሚገኙ ሌሎች ብሄረስቦች አማራ 580,353፥ ትግራይ ትግርኝ 15,673፥ ቤጃ 1,595፥ ሲዳማ 6,787፥ ከፋ 339፥ ፈላሻ 1,126፥ ናራ 593፥ አድሬ 974፥ ወላይታ 8,484፥ አርጎባ 366፥ ዘይሴ 373፥ ጉራጌ 64,756፥ ኩናማ 4,861፥ ዳስነች 1,320፥ ሀድያ 3,178፥ ከምባታ 3,197፥ ፀማይ 625፥ ዳውሮ 1,723፥ ኮንሶ 601፥ ሀመር 1,500፥ ወዘተ…ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በ1977-1978 በተካሄደው የሠፈራ ፕሮግራም መሠረት በስግስጋ 176,849 በኩታ ገጠም 126,953 የሚደርሱ የተለያዩ የብሄረስብ አባላት በኦሮሞ መሀል ማለት ወለጋ፥ ኢሉባቦርና ከፋ ሠፍረዋል። ኦሮሞ የሰፈረበት መሬት በአብዛኛው ደጋማ ለም፥ ስፊና ሜዳማ በመሆኑ ለእንስሳት እርባታና ለእርሻ ተስማሚ ነው። የህዝቡ ብዛት በ1976 በተካሄደው የህዝብና የቤት ቆጠራ መረጃ መስረት 12,471,131 ሆኗል። አብዛኛው የኦሮሞ ብሄረብ አባሎች በመሀል አገር በእርሻ፥ በአንስሳት አርባታ፥ በዕደ ጥበብና በንግድ ይተዳደራሉ። በደቡብ-ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ገና በዝቅተኛ ዕድገት ላይ የሚገኙ የኦሮሞ ዘምድ ብድኖች በዘላንነት ይኖራሉ።*

በወያኔ የአምባገነን ሥርዓት በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተው ክልል በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተወሰነ ደረጃ ተከባብረውና ተቻችለው አብረው የኖሩ ብሄረሰቦችን ለብዙ ችግርና መከራ ዳርጓቸዋል። ከሦስትና አራት ትውልድ በላይ ሀብት አፍረተውና ቤተሰብ መስረተው ከኖሩበት ስፍራ በግድ ወደ ድሮ የመጣችሁበት ክልላችሁ ሂዱ ተብለው እንዲፈናቀሉና ከተሞችን እንዲያጥለቀልቁ ሆኖአል። የኦሮሞ ፍልስትና ስርጭት በተመለከተ እንደ ፕሮፌስር መሀመድ ሀሰን በመጽሐፋቸው "ኦሮሞ በኢትዮጵያ" (The Oromo of Ethiopia: A History 1585-1860) ገለጻ

ከትልቁ የኦሮሞ ፍልስት በፊት በመሃል አገር ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ በእርሻና በከብት አርቢነት ለብዙ መቶ አመታት እንደኖረ ያወሳሉ። የብሄረሰብ ኢንስቲትዩትም ትልቁን ፍልስቱን እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

*በአስራ ስድስተኛው ምዕተ አመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በ ኢማም አህመድ ግራኝና በልብነ ድንግል 1508-1540 ማሀል የተደረገው ጦርነት ከተፈጸመ በኋላ ከ1540-1632 ባለው ጊዜ ውስጥ የኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት ከደቡብ ኢትዮጵያ በመነሳት በምስራቅ በማሀልና በምዕራብ ኢትዮጵያ በተለያየ አቅጣጫ እየተመሙና እየተዋጉ ለምና ነፋሻ የሆኑ ደጋማ ቦታዎችን በመያዝ ሰፍረዋል።...በፍልስታቸው ጊዜ የአጓዳኛቸውን ብሄረሰቦች ስርአቶች ሲቀበሉ የተቀሩት ደግሞ የሌሎችን ማሀበራዊ አደረጃጀት በመቀበል ፋንታ የራሳቸውን የገዳ ስርአት በሌሎች ላይ ለማስፈን ችለዋል። ኦሮሞ በገዳ ሥርዓት እየተመራ ለብዙ ዘመን ኖሯል።* በአጠቃላይ የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለውና ለአንድነታችንና ለጋራ እሴቶቻችን መዳበር ትልቅ አስተዋፆ ያደረገ ሕዝብ ነው። የኢንስቲትዩቱ ጥናትም በማከል እንዲህ ይላል፡

*የወሎ ኦሮሞዎች በመማሀል ደጋ ኢትዮጵያ ከአማራ፡ ከአገውና ከትግራይ ብሄረቦች ጋር ተቀላቅለዋል። የቱልማ፡ የጅሌ፡ የከረዩና የሜጫ ኦሮሞዎች ከሸዋ አማራና ከአፋር ጋር በመጎራበት፡ እንዲሁም የኢቱ ኦሮሞዎች በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሱማሌ፡ ከአርጎባና ከአፋር ጋር በመዋሰን፡ የአርሲ ኦሮሞዎች በደቡብ ከሀድያና ከጉራጌ ጋር በመስባጠር፡ እንዲሁም የጉጂና የቦረና ኦሮሞዎች በደቡብ ከሶማሌ፡ ከሲዳማ፡ ከጌድኦ፡ ከቡርጂና ከኮንሶ ጋር በመጓደን፤ የሜጫ ኦሮሞዎች ደግሞ ወደ ምዕራብ በመዝለቅና በምዕራብ ከሚኖሩ የኢትዮጵያ*

ብሄረሰቦች ከአናርያ፣ ከቦሻ፣ ከከፋ፣ ከሞቻና ከአንፊሎ ማህበረሰቦች ጋር በመጎራበት፣ በመጋባትና በመወራረስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት...ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የኦሮምኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ቋንቋዎች አንዱ ነው። በታሪክ እንደተመዘገበው በዘመነ መሳፍንት በጎንደር ቤተ መንግስት አማርኛን በመተካት የቤተ መንግስትና የወታደሩ ቋንቋ ለመሆን ችሎ ነበር። በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በውጭ ሚስዮናውያንና በአንዳንድ የብሄረሰቡ ምሁራን ጥረት መጽሀፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ፊደል ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ ተተርጉሟል። ከ66ቱ አብዮት በኋላም በኦሮምኛ መስረተ ትምህርት፣ ጋዜጣ መታተምና የሬዲዮ ፕሮግራም መስራጨት ጀምሮ ነበር።

በወያኔ አምባገነን ዘመን የኦሮሞኛ ቋንቋ የሚጠቀምበት ፊደል የግዕዝ መሆኑ ቀርቶ በላቲን ፊደል ማለት ቁቤ እንዲሆን ተደርጓል። ይህ የፊደል ለውጥ ወደፊት ጥቅሙንና ጉዳቱን በሂደት ታይቶ በኦሮሞ ሕዝብ የሚወስን ጉዳይ ይሆናል። የኦሮሞ
ሕዝብ ላቲን ወይም በግዕዝ ይሁን የሚለውን ውሳኔ መቀበል ግዴታችን ነው። ብሄረሰቦች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በሚያውቁት አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ መደረጉ የመማርና የማስተማር ሂደቱን ያፈጥናል ብለን እናምናለን። እንደግፋለን። ያም ሆኖ የብሄራዊ ቋንቋ አማርኛ ቢያንስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ቢሰጥ
ለተማሪዎቹ ወደፊት በፈለጉት በማንኛውም ስፍራ የመስራት እድላቸውን ያስፋዋል ማለት በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል ብለን እናስባለን።

## ለ. የአማራ ሕዝብ

የአማራ ሕዝብ እንደአቻው እንደ ኦሮሞ ሕዝብ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ነው። ዛሬ አማራ ተብሎ የሚጠራው ስሜን ሸዋ፣ ከጥቂት ምስራቃዊ ወረዳዎች በቀር መላው ወሎን፣ ከምዕራብ ጠረፎች በቀር ጎጃምንና ጎንደርን በሙሉ ይሸፍናል። አማርኛ ተናጋሪ ብሄረሰቦች አንድነትና ልዩነት ያላቸው ናቸው። አንድነታቸው ኢትዮጵያዊነትና የአማርኛ ተናጋሪ መሆናቸው ነው። ልዩነታቸው እንደቀረው ብሄረሰቦች ሁሉ እራሳቸው የሚቀበሉትና የሚያምኑበት መጠሪያ ስም አላቸው።

ለምሳሌ ወሎ ክፍለ አገር የሚኖር ወሎዬ፡ ጎንደር ጎንደሬ፡ ጎጃም ጎጃሜና ሸዋ ሸዌ ተብለው መጠራትን ይመርጣሉ፡፡ ተጨፍልቃችሁ በአንድ አማራ ክልል ውስጥ ሁኑ መጠሪያችሁም ከዛሬ ጅምሮ አማራ ነው አባባል ብዙም አይዋጥላቸውም። ለምሳሌ በወሎ አማራ ማለት ክርስቲያን ማለት አድረገው ነው የሚያዩት፡ የወሎ ሕዝብ አብዛኛው እስልምና ተከታይ በመሆኑ አማራ ተብሎ መጠራቱን አይወደውም። ያም ሆኖ አማርኛ ተናጋሪ በመሆኑ አያፍርበትም። በእርግጥ በአለፈው ሥርዓት በተለይ በንጉሱ ዘመን ከተለያዩ የብሄረስቦች ገዢ መደቦች ውስጥ "አማራው" ትልቅ ድርሻ ነበረው ማለት ይቻላል። ጉዳዩን በሁለንተናዊ ገጽታው ከተመለከትነው ማለት የብሄረስቦች ላይ የነበረውን የባህልና የሀይማኖት ጭቆናዎች ባሻገር በብሄረስቦች መካከል የመደብ ጭቆና ማለት ሀብታምና ደሃ መካከል ቅራኔ ነበር። ግራም ነፈስ ቀኝ ወደፊት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚመሰረትበት ጊዜ እነዚህ ክፍላተ አገሮች አሁን እንዳለው የአማራ ክልል እንዲሆን በባህልም፡ በመልካ ምድርና በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ይሆናሉ ከተባለና የሕዝብ ይሁንታ ካገኘ የማይሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ግን የወያኔ ተለጣፊዎችና አፈቀላጤ ምሳሌ እንደነ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ መስል "በማር የተለወሰ ኮሶ" ዓይነት ምክር "የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት" አማራነቱን የረሳ ሕዝብ በመጀመሪያ በአማራነቱ ጥቅሙንና መብቱና ማስከበር አለበት ከዚያ በኋላ ወደ ኢትዮጵያዊነት ሊመጣ ወይም ሊገባ ይገባል የሚለው ምክር በፍጹም ተቀባይነት አይኖረውም። የአማራው ብሄረስብ ምርጫው በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊነቱን አስቀድመው በሁለተኛ ደረጃ የመጣበትን ክፍላተ አገር ከዚያም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ አውራጃና ወረዳ እንዲሁም ጎጥ መገለጫነት መውረድ ነው። ይህም መብቱ እንደሌሎች መብታችን ይከበርልን እንደሚሉት እንደ ትንሿ ሐረሪ ሳትቀር በክልል ደራጃ ስትመደብ እነዚህ አራት ትልልቅ ክፍላተ አገር የነበሩ ተጨፍልቀው አንድ ክልል እንዲሆን ለምን አስፈለገ? ያለ ሕዝብ ይሁንታ ለምንስ ከወሎና ከጎንደር መሬት ተቆርሶ ወደ ትግራይ ክልል እንዲጨመር ተደረገ? ሸዋም ለሁለት ተከፍሎ ስሜኑ ወደ አማራው ክልል ደቡቡ ወደ ኦሮሞ ክልል እንዲቀላቀል ለምን ተደረገ? እነዚህን መስል ጥያቄዎች ከስሜታዊነት በፀዳ መንፈስ ወደ ፊት መልስ የሚፈልጉ ናቸው ማለት ነው።

እንደ የኢትዮጵያ ኢንስቲትዩቱ ጥናት የአማራ ሕዝብ ተብሎ የሚጠራውን የሚያካልሉና በውስጡ የሚገኙ ብሄረሰቦች አማራው ጋር ያላቸው ግንኙነት እንደሚከተለው ነው።

*…ብሄረሰቡ በደቡብ ኦሮሞን፡ በምስራቅ አፋርን፡ በሰሜን ምስራቅ ትግራይ ትግሪኝና አገውን፡ በሰሜን-ምዕራብ ጉሙዝና አገውን፡ በደቡብ ምዕራብ ሽናሻን የጉሙዝ ብሄረሰብን ይጎራበታል። በ1976 በተካሄከው የህዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት የአማራ ህዝብ ብዛት 11,944,204 ነው። ወይጦ፡ ቅማንትና ፈላሻ በከፊል በመታቀፍ ወይም በሙሉ በመከብብ በአማራ ብሄረሰብ ማሃል በተናጠል ሰፍረው ይገኛሉ። እንዲሁም ሌሎች ብሄሰቦች ኦሮሞ 90,229፡ ትግራይና ኤርትራ 14,8024፡ አርጎባ 2,595፡ ጉራጌ 4,001፡ ትግረ 595 በዚህ አማራ በኖርበት ክልል ውስጥ ተሰራጭተው አብረው ይኖራሉ።*

የአማራ ብሄረሰብ ታሪካዊ መነሻው በወሎ ክፍለ ህገር በቦረና አውራጃ ልዩ ሰሙ "አማራ ሳይንት" የተባለው ወረዳ ነው። ከ13ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በደቡብ መርሃቤቴ፡ በምስራቅ ይፋትና አንጎ፡ በሰሜን ቤጌምድር፡ በምዕራብ ጎጃም የሚያዋስኑት አማራ የሚባል አውራጃ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል። በአውሮፓ የኢትዮጵያ ጥናት መስራች የሆነው ኢትዮጵያዊው አባ ጎርጎርዮስ በበኩሉ ሐምሌ 1643 ዓ.ም. ለኢዮብ ሎዶልፍ በጻፈው ደብዳቤ የአምሀራን አውራጃ እንደሚከተው ገልጾታል። *"አምሀራ አንድ ጎኑ በሰሜን በጌምድርን ይነካል። የሚለየው በሽሎ የሚባለው ትልቅ ወንዝ ነው። በስተደቡብ ለላው ጎኑ ከሽዋ ግዛት ጋር ይዋሰናል። ከሱም የሚለየው የወንጭት ወንዝ ነው። ከአውራጃዎቹ ሁሉ አምሀራ ከፍ ይላል። ከሁሉም ይበልጣል፡ በአጭሩ የአምሀራ አቀማመጥ ይህ ነው።"*

አሁን ወንዞቹ ደርቀዋል አልያም ስማቸው ተቀይሯል ማለት ነው። በታሪካዊ አገር ግንባታ ሂደት የአማራ ሳይንት ብሄረሰብ በመፍለስና በመስፋፋት ጎንደርን፡ ጎጃምን፡ ወሎንና ስሜን ሽዋን የአማርኛ ቋንቋና ባህል ተከታይ ለማድረግ ችሏል ማለት ነው። ይህ ማለት በእነሱ መካከል አንድነትና ልዩነት የለም ማለት አይደለም። ሌላው ቀርቶ በባልና ሚስት መካከል አንድነትና ልዩነት ያለ ነገር ነው። አብዛኛው ሕዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ኢኮኖሚ፡ በእደ ጥበብ፡ በንግድ ወዘተ… ነው። ባለፈው ዘመን የአማራ ገዥ መደብ አባላት በአስተዳደር፡

በዳኝነትና በምስለኔነት ስራ ሲሰማሩ፡ የብሄረሰቡ ጭቁን አባላት ነፍጠኛ/ወታደርነት፡ ቀላጤ፡ ጭቃ ሹምና ቋሚ ለጓሚ
እየሆኑ ኖረዋል። ልዩነታቸው ከእርስ በርሳቸው አንድነት በተጨማሪ ጎንደሬው ለትግሬና ለኤርትራው፡ ጎጃሙ ለጎንደርና ለወሎ እንዲሁም ሸዋ ለኦሮሞውና ለትግሬው እንደአጎራባችነታቸው አንዱ የሌላውን ቋንቋ ይናገራል እንዲሁም በስነልቦና በአመለካከት የሚቀራረብበትን ሲያንጸባርቁ ይታያል። የወሎ ክፍለ አገርን ብንወስድ ከሁሉም ልዩ የሚያደርገው የሁሉም ብሄረሰቦችና እምነቶች መገናኛ የሆነና አብሮ ተቻችሎ የመኖር ለቀሪው የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ተምሳሌነት ተጠቃሽ በመሆኑ ነው።

የአማራው ብሄረሰብ እንደ ኢንስቲትዩቱ ገለጻ፡

*የብሄረሰቡ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን ከሰርው ልሳን አንጻር የሴማዊ ቋንቋ ቤተሰብ ነው። አባላቱ በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚነገሩ እንደ ኦሮሞኛና ትግርኛ ያሉ ቋንቋዎች በሁለተኛ ደረጃ በጥቂቱ ይናገራሉ። የአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ ላይ ከዋለ ስድስት መቶ ዓመታት ሆኖታል። ለመጀመሪያ ጊዜ በ14ኛው መቶ አመት ተቀርጸ የተገኘው የአማርኛ ጽሁፍ እጅግ ጥቂት ነው። የጽሁፉ ዓይነት ደራሲው ካልታወቀ ለነጋሚዎች የገጠመ ቅኔ ነው። ቅኔው በዘመናት ውስጥ አንድ ቋንቋ እየተለዋወጠ ለመሄዱ ምስከር ከመሆኑ በላይ ዛሬ የማንናገረው፡ የማንጽፈውና ለመረዳት የማንችለው የሰዋስው አካሄድና የቃላት አገባብ አለበት። አማርኛ እንደገና ለ300 አመታት ያህል ሳይጻፍ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ በ17ኛው መቶ ዓመት ብቅ አለ። እንደዚህ ሲወድቅ ሲነሳ ኖሮ በ19ኛው መቶ ዘመን አፄ ቴዎድሮስ የመንግስታቸው ይፋ ቋንቋ ሲያደርጉት አማርኛ የግዕዝ ቦታን በመያዝ የመንግሥት ጉዳይ የሚከናወንበት የጽሁፍ ቋንቋ ሆኗል። በ20ኛው መቶ ዓመት መግቢያ ላይ እድገቱ እየተፋጠነ ሄዶ ጋዜጣ ተጽፎበትና ልብ ወለድ ተደርሶበታል። ብሎም በህግና በፖሊሲ እየተደገፈ አድጓል።*

## *ሐ. የትግራይ ሕዝብ*

የትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት አንፃር ሲታይ በቁጥር አነስተኛ ወይም መካከለኛው ደረጃ ይመደባል። ሆኖም ይህ አካባቢ በጥንት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት 500 ምዕተ ዓለም ጀምሮ ትግራይ ትግርኛ ማለትም የትግራይና የኤርትራ ሕዝቦች የሚያጠቃልል

የኢትዮጵያ የስልጣኔ እንብርት በመሆኑ እንዲሁም ትልልቅ በዓለም ላይ ካሉት ሃይማኖቶች ማለት ኦሪት፣ ክርስትና እስልምና ወደ አገራችን የገባበት በር ነው። ትግራይ ሕዝብም ያፈራቸው ምሁራን የኢትዮጵያ የሙዚቃው
(አባት) ሊቅ እንደያሬድ (composer) የሙዚቃ ቃናን ግዕዝ፣ አራራይና ዕዝል ብሎ የከፋፈለ እንዲሁም እንደዘርያቆብ ያለ ፈላስፋ አውሮጳ በጨለማ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ስለተፈጥሮ፣ ስለፍርድና ስለ እውነትና ውሸት እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች የጥናት ምርምር ያደረጉትን ያፈራ ነው። ብሄረሰቡም ጥንታዊ የኢትዮጵያ
መንግስት የተመሰረተበትን አካባቢ ያቅፋል። (ይህን ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንደ ትልቅ ብሄረሰብ አድርገን ለመመደብ መርጠናል።) ? ይህ ለምን አስፈለገ? እንደ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ገለጻ፣

*የትግራይና ኤርትራ ኅብረተሰቡ በሚኖርበት አካባቢ በየጊዜው የቅድመ ታሪክ የጥንት ታሪክ ቅርሶች ይገኛሉ። የብሄረሰቡ መኖሪያ ክልል የጥንት ስልጣኔ ባድማ ነው። ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ በቀይ ባህር፣ በአባይ ሸለቆና በህንድ ውቅያኖስ ጠረፎች በተከታታይ የተነሱ የውጭ ሃይሎች ቱርኮች፣ ፓርቱጋሎች፣ ግብጾች በ19ኛው ምዕት ዓመት በቅኝ ገዥነት የዘመቱ ፈረንሳዮች፣ እንግሊዞችና ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር በሞከሩበት ጊዜ ሁሉ...በር ጠባቂና ጥቃት መካች በመሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ለ86 ዓመታት በኢትዮጵያ ሰፍኖ በነበረው በመሳፍንት ዘመን ከትግራይ ትግርኝ ብሄረሰብ መሀል ታላላቅ መሳፍንት እንደነ ስሁል ሚካኤል (1740-1780)፣ ወልደ ስላሴ (1788-1816)፣ ሰባጋዲስ (1818-1831)፣ ውቤ (1831-1855) የመሳሰሉ እየተነሱ ከፍተኛ ስልጣን ለመጨበጥና ያጤዎች ሞግዚት ለመሆን ችለዋል።*

የትግራይ ክፍለ አገር ወይም በአሁኑ ክልል በስሜን ኤርትራን፣ በደብቡ አማራ፣ ኦሮሞን፣ በምሥራቅ አፋር፣ በስሜን ምስራቅ ሳሆና አሳውርታ ያጎራብቱታል። የሕዝቡም ብዛት እንደ 1978 የሕዝብ ቆጠራ 4,107,687 ነው። የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በኤርትራ አካለጉዛይ፣ ህማሴንና ሰራዬ አውራጃዎች እንዲሁም መላውን ትግራይ ያካትታል። ትግርኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ካሉ የጽሁፍ ቋንቋዎች አንዱ ነው። በደርግ ዘመን ቋንቋው በብሄራዊ ሬድዮን ይተላለፍና ጋዜጣም ይታተምበት እንዲሁም መስረተ ትምህርት መጻሕፍት ተዘጋጅቶ ይስጥበት ነበር።

ሕዝቡም የሚተዳደረው በእርሻ፣ በእንስሳት ርባታ፣ በእደ ጥበብና በንግድ ሥራዎች ነው።

## *በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙት ብሄረሰቦች*

### *1. አፋር ሕዝብ*

የአፋር ሕዝብ ከአራት ቦታ ተከፋፍሎ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ የአፋር ክልል ከሚባለው ሌላ ቁጥሩ በዛ ያለ የአፋር ሕዝብ በጅቡቲ፣ በኤርትራ፣ በትግራይ ይገኛል። ሕዝቡም የሚተዳደረው በከብት አርቢነትና አሣ አጥማጅነት ነው። በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ሕዝብ ነው። የአፋር አካባቢ በተለይም የስምጥ ሸለቆ (rift valley) ጥንታዊ ግኝቶች በተለይም የቀድሞ ሰዎች አጽም ማለት እንደ ድንቅነሽ አይነት የተገኘበት ነው። የኢትዮጵያ ኢንስቲትዩት የአፋርን ሕዝብ እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

*አፋር ብሄረሰብ "አዳል፣ ደንከል፣ ጠልጣል" በሚባሉ ሌሎች ስሞችም ይታወቃል። አፋር በስሩ ለጠቃለሉ የሚችሉ ብዙ ዝምድ ቡድኖች አሉት። ብሄረሰቡ በአሰብ አስተዳደር በአሰብ አውራጃ፣ በወሎ ክ/ሀገር በአውሳ አውራጃ፣ በሸዋ ክ/ሀገር በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ፣ በቡረሞዳይቶ ወረዳ፣ በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በዱለቻ ወረዳ፣ በሀረርጌ ክ/ሀገር በጨርጨር አዳልና ጋራ ጉራቻ አውራጃ፣ በገዋኔና በምስራቅ አዋሽ ወረዳዎች፣ በትግራይ ክፍል ሀገር በሁለት አውላሎ አውራጃ በበራህሌ ወረዳ፣ በእንደርታ አውራጃ በሸሸት ወረዳ፣ በራያና አዘቦ አውራጃ በዲዲግስዐለ ወረዳ፣ በኢጋሜ አውራጃ በዳሎል ወረዳ ይኖራል። በዚህ የአፋር ብሄረሰብ በጥቅል በስፈረበት አድያም ውስጥ አማራ 21,546፣ ትግራይ ትግሪኝ 1,073፣ ኦሮሞ 47,769፣ አርጎባ 452 ይኖራሉ። የአፋር ብሄረሰብን በስሜን-ምስራቅ ቀይ ባህር፣ በምዕራብ የትግራይ ትግርኝ፣ የአማራና የኦሮሞ ብሄረሰቦች፣ በደቡብ የኦሮሞና የኢሳ ብሄረሰቦች ያዋስኑታል። የአፋር ህዝብ ብዛት 490,716 ነው።*

በአጠቃላይ የአፋር ሕዝብ የአጎራባች ብሄረሰቦች ቋንቋዎችን ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ኦሮሞኛ፣ ሱማልኛን በሁለተኛ ደረጃ ይናገራል። በአሁኑ ጊዜ የአፋር ሕዝብ በተለያየ ድርጅቶ ተደራጅቶ እንቢኝ በወያኔ አምባገነን አልገዛም ማለት ለመብቱ፣ ለነፃነቱና የዘመናዊ እርሻ ብዝበዛ በሁለገብ ትግል በመቃወም ላይ ይገኛል።

## *2. ሲዳማ ሕዝብ*

የሲዳማ ሕዝብ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖር ነው። በውስጡም ብዙ ሐይቆች ማለት እንደ ላንጋኖ፡ ዝዋይ፡ አብያ፡ የመሳሰሉት የብዙ የውጭና የአገር ውስጥ ጎብኞች የሚያዘወትሩበት ስፍራ ነው። በሐይቆቹም አካባቢ ብዙ የተለያዩ አውአፋት (የወፍ አይነቶች) አሳነባሪ፡ ጉማሬና ዘንዶች ይገኛሉ። በዋና የሚታወቅበት በአለም ደረጃ ብናው አይነት ነው። የሲዳማን ብሄረሰብን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ኢንስቲትዩት እንዲህ ይላል።

*የሲዳም ብሄረሰብ የሚኖረው በሲዳሞ ክፍለ አገር በሲዳማ አውራጃ ነው። ብሄረስብን በሰሜን፡ በምስራቅና በደቡብ ኦሮሞ፡ በምዕራብ ወላይታ፡ ቡርጂና ጌዶ ያጎራብቱታል። የሲዳማ ሕዝብ ብዛት 1,297,419 ሆኗል። በብሄረስብ ማህል አማራ (62738)፡ ትግራይ ትግርኛ ማለት ትግራይና ኤርትራ (40230)፡ ከንባታ (3783)፡*
*ሃድያ (2445) ይኖራሉ። የብሄረሰቡ ቋንቋ ሲዳምኛ፤ ተናጋሪዎቹ ቋንቋቸውን "ሲዳሞ ቃሌ" ወይም "ሲዳሞ አፍ" ብለው ይጠሪታል። ብሄረስብም በሁለተኛ ደረጃ ኦሮምኛ፡ አማርኛ፡ ጌዲኦኛና ወላይትኛ በየአውራጃው ጠረግፍ ይናገራሉ። ሲዳምኛ ፊደል ተቀርጾለት መስረተ ትምህርት ይስጥበታል።*

የሲዳማ ሕዝብ ታሪካዊ አመጣጥ በጽሁፍ ተመዝግቦም ባይገኝ ብዙ ምንጮች ከአያት ቅድመ አያት በአፊ ታሪክነት በአዛውንት የሚነገር አሳማኝ እንደ ብዙዎቹ አፍሪካ አገሮች ታሪክ አለው። ለመጠቃቀስ "ስዳማዎች ጥንት ከምስራቅ ኢትዮጵያ
በኩል ለከብት ርቢ የሚሆናቸውን አካባቢ ለመምረጥ ሲዞሩ አሁን ወደሚገኙበት ስፍራ መድረሳቸውን ይነገራል።...ሌላው የሲዳማ ሕዝብ ከሚኖርበት ከስሜን ወደ ደቡብ ለም መሬት ተስደደ የሚል ነው። ብሄረስቡም ከኦሮሞ ገዳ ጋር የሚመሳስል የአስተዳደር ሥርዓት እንደ ነበረው ይነገራል፡ ግን መቼ ሥርዓቱ በሲዳማ ህብረተስብ ውስጥ እንደተጀመረ በውል አይታወቅም። ይህ በገዳ ሥርዓት ላይ የተመስረተው አመራር በሎዋ ይባላል። አንድ የሲዳማ ተወላጅ በአርባ አመቱ በፊት በሎዋ ካልደረስው አይገረዝ...አንድ በሎዋ አርባ አመት በአምስት ንኡሳን እንያንዳንዳቸው ስምንት አመት የስልጣን የሚቆይበት ጊዜ ይሆናል። ይህ የገዳ ሥርዓት የሚያኮራ ኢትዮጵያዊ እሴት ነው። ወደፊትም ዳብሮ ከአንዳንድ ዘመናዊ አስተሳስቦች

በመጨመር በጋራ ትግላችን በሚመሰረተው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አካል መሆን ያለበት ነው።

## 3. ሃድያ ሕዝብ

የሃድያ ሕዝብ በጥንታዊት ኢትዮጵያ በእራስ አገዛዝነት በማዕከላዊ ፌደራል አስተዳደር ማለት በንጉስ ነገስት ስር የሚተዳደር ብሄረስብ እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል። በ13ኛው ክፍለ ዘመን ልክ ኦሮሞዎች በዘመነ መሳፍንት በቤተ መንግስት አካባቢ በብዛት ይታዩ እንደነበር ሀድያዎች በቤተ መንግሥት በወታደርነት በብዛት ይገኙ ነበር። የሀድያ ተወላጅ የሆነችው ብልሂቱ ንግስት እሌኒ የንጉስ አምደ ጽዮን አማካሪ ለመሆን በቅታ ነበር። የኢትዮጵያ ብሄረስብ ኢንስቲትዩት ጥናት እንዲህ ይላል፡፡

*ሀድያ በ1316 ለአፄ አምደፅዮን (1314-1344) ከገበረ በኋላ ወታደር ሲመለመልበት ቆይቷል። በሌላው ወቅት የይፋት ገዢ በአምደፅዮን ላይ በአመጹ ጊዜ የሀዲያው ገዢ አምሮ የይፋትን ገዢ በመርዳት አፄ አምደፅዮን ወግቷል። ግን ሁለቱም በመሸነፋቸው ሀዲያ እንደገና በአምደጽዮን ስር ወደቀ። ሌላው የሀድያ ገዥ ማሂሎ በዘርዓያዕቆብ (1334-1468) ላይ በማመጽ ድል መሆኑ ተዘግቧል። እንዲሁም በልብነ ድንግል (1508-1540)፡ በገላውዲዎስ (1544-1559)፡ በሰርፀ ድንግል (1563-1597) ዘመን ሀዲያ እያመጸ በየጊዜው ድል መሆኑ ተጽፏል።*

የሀድያ ሕዝብ በግቤ በስተስሜን ያለው አካባቢው በኦሮሞ በ17ኛው መቶ አመት ከተያዘ በኋላ ለአጭር ጊዜ ከደጋው ማዕከላዊ መንግስት ተለይቶ ነበር። የሽምጥ
ሽለቆ አካባቢም በአርሲ ኦሮሞዎች ከመያዙ በፊት በሃድያ ስር እንደነበር ይነገራል። በአጭሩ የሀድያን ሕዝብ አስመልክቶ የብሄረሰብ ኢንስቲትዩቱ የሚከተለውን አስፍሯል፡

*ሀድያ በጥንት ዘመን "ጉዴላ" በመባል ይታውቃል። በውስጡ የተወሰኑ ዘምድ ቡድኖች ይታቀፋሉ። ብሔረሰቡ በሸዋ ክፍለ አገር፡ በከምባታና ሀድያ አውራጃ፡ በሲቆና በጥምባሮ፡ በሊሙ፡ በክንተብ፡ በኦሞ ሸለቆ ወረዳዎች ይኖራል። ሀድያ በሚኖርበት ክልል ውስጥ አማራ (22,329)፡ ትግራይና ኤርትራ (675)፡ ኦሮሞ (16,068) በስርጭት ስፍረው አብረው ይኖራሉ። ብሂረሰብን በስሜንና በምስራቅ ጉራጌ፡ በምዕራብ የምሳ፡*

*በደቡብ ምስራቅ ጥምባሮ፣ በደቡብ ከምባታ ይጎራብቱታል። የሕዝቡ ብዛት 649,398 ነው።*

*የብሔረሰቡ ቋንቋ ሀዳይኛ ሲሆን የኩሽ የቋንቋ ቤተሰብ ነው። ብሔረሰቡ በሁለተኛ ደረጃ ከምባጥኛን፣ ኦሮምኛን፣ አማርኛን፣ ወላይተኛንና ስልጢኛን በየወሰኑ ዳርቻ ይናገራል። ቋንቋው በ1924 በጽሁፍ ላይ እንደዋለ ይገመታል። ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ በጎልማሶች ትምህርት መምሪያ የመሰረተ ትምህርት ማስተማሪያ መጻህፍት በቋንቋው ተዘጋጅቶ ለማስተማሪያነት እንዲውል ተደርጓል። ታላላቅ አዋጆችና የመንግስት መመሪያዎች በቋንቋው በሬዲዮ ይሰራጫል።*

## *<u>አናሳ የተረሱት ብሄረሰቦች</u>*

የአናሳ የተረሱ ብሄረሰቦች በተለምዶ የዳር አገር ተብለው የሚጠሩትን አካባቢ የሚመለከት ነው። እነኝህ ብሄረሰቦች በአለፉት ሥርዓቶች እንደማንኛውም የአገሪቱ ዜጋ የሚጠበቅባቸውን የትምህርት፣ የጤና እንዲሁም ሌሎች ታክስ ይከፍላሉ ግን ምንም አይነት ማህበራዊ አገልግሎትና ልማት ያልደረሰው አካባቢ ነው። አንዳንዶቹም መኖራቸው አይታወቅም ነበር። እነዚህ አናሳ የተረሱ ብሄረሰቦች ይጠቀሙም አይጠቀሙም በደርግ ዘመን እውቅና አግኝተው ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ያሉበት ጊዜ ነበር። ከእነሱም ኮምሳ፣ አርባሬ፣ አሪ፣ ባስኬት፣ ጫራ፣ ጀብላዊ፣ ዳስነች፣ ዲዚ፣ ገዋዳ፣ ጊዶሌ፣ ካሮ፣ ኮይራ፣ መኤን፣ ማኦ፣ ሞቻ፣ ኦይዳ፣ ቅማንት፣ ሼ፣ ሺናሻ፣ ሱሪ፣ ጥንባሮ፣ ወይጦ፣ የምሳ...ወዘተ ናቸው። እንደሚታወስው በጋምቤላ ክልል በሚኖሩ ሁለት ብሄረሰቦች ማለት በአኝዋክና በመዠንግር መካከል በወያኔ ስራሽ ብጥብጥ ብዙ ሕዝብ እንዲያልቅ ሆኖአል። እዚህ ላይ እስከ ደርግ ዘመን እንደው በጭራሽ ስማቸው ተሰምቶ የማይታወቁ የተረሱ ብሄረሰቦች መካከል አንድ ሦስቱን እናቀርባለን።

### *<u>5. የዳስነች ብሄረሰብ</u>*

ይህ ማህበረሰብ እራሱን ዳስነች ብሎ ይጠራል። የሚገኘውም በገሞጉፋ ክፍለ አገር በገለብና ሀመር ባኮ አውራጃ በገለብ ወረዳ በሽምጥ ሽለቆ ቆላ ከቱርካና ሀይቅ በስተስሜን፣ በኦሞ ወንዝ ዳርቻ ነው። የሕዝቡም ብዛት 25832 ነው። ቋንቋውም

ዳስንችኛ ይባላል። ቋንቋው ገና በንግግር ደረጃ ላይ ያለ ፊደል ያልተቀረጸለት ነው። የሚተዳደረው በእርሻና በከብት እርቢነት ነው። በምግብ አጠቃቀም የግመል ወተት የተለመደ ነው።

በዳስነች ባህል ጎጂ ገጽታዎች አሉ። ለምሳሌ ሴቶች ከንፈራቸውን እየተበሱ ጌጥ ያንጠለጥሉበታል። ወንዶችና ሴቶች የተለያየ ቀለም ያለው አፈር በቅቤና በእጣን እያቦኩ ስውነታቸውንና ፀጉራቸውን ይቀባሉ።...አንድ ወንድ ልጅ ከወጣትነት ወደ ጎልማሳነት በሚሸጋገርበት ወቅት ማለት በግርዛት ጊዜ በሬ ታርዶ በዓል ይደረግለታል። አንዳንድ ወንዶች ለመገረዝ ፈቃደኛ ካልሆኑ ለሴቶች በሚዘጋጀው የአቅመ ሄዋን ማወጃ የጭፈራ በዓል እንዲካፈሉ ይደረጋሉ። ጋብቻ በጥቅም ላይ የተመሰረተ ነው። ጋብቻ የሚከናወነው በከብት ጥሎች በወንዱ ልጅ ወላጆች ለሴቷ ልጅ በሚቀርበው ጥያቄ መስረት ይከናወናል።...የዳስነች ህብረተሰብ መብትና ግዴታ በእድሜ ጠገግ ላይ የተመሰረተ ነው። ማህበራዊ ችግሮች በሽማግሌ ሸንጎዎች በውይይት ይፈታሉ። ንግግር በእድሜ ተዋረድ ከአንጋፋ ሽማግሌ ተጀምሮ ወደ ጎልማሳው ይሄዳል።...የጉባዔ መሪም ጄሌብ ይባላል፣ የሚመረጠውም በንግግር ችሎታውና በአስተሳሰቡ ነው።...በዳስነች ማህበረሰብ የዝምድ ቡድን አለቆች ሁሉ የጃሌባ ተጠሪዎች ይሆናሉ፣... በህብረተሰቡም ስም የአምልኮት ተግባራት ማካሄድና ሞራ እያነበቡ መተንበይ መቻል አለባቸው። በዳስንች ባህል ስው አውቆ የገደለ ተደብድቦ ይገደላል። በስህተት የገደለ ግን ወደ ጫካ ገብቶ ፀጉሩን ተላጭቶ የሚቹን ቤተሰብ ይቅርታ ከጠየቀ ከህብረተሰቡ ጋር መቀላቀል ይችላል። (ገጽ 21-22)

## 6. የጀብላዊ ብሄረሰብ

ጃብላዊ በተለያዩ አማራጭ ስሞች ይጠራሉ። በርታ፣ ቤንሻንጉል፣ ዉጣዉጥ፣ ፋዶን፣ በጋሌና ሆጃሌ ናቸው። ... አካባቢው "ሆጃሌ፣ ኮጅሌ፣ ወይም ሆገሌ" የሚለውን መጠሪያ ያገኘው በ1898 የበርታ ግዛት ኢትዮጵያ መንግስት ግዛት ስር ከሆነ በኋላ አሶሳን አጠቃሎ ከገዛው የሪካብያ ቤተሰብ ከነበረው ከሼህ ሎጃሌ አል ሀስን ስም ነው። በ1821 የግብፅ መሪ የነበረው መህመድ አሊ የፎንቀላና የካርቱም ነዋሪዎችን በማስቃየቱ በአካባቢው ይኖሩና የአረብ ዝርያዎች ነን የሚሉ ቡድኖች ሸሽተው መጥተው በበርታ ተራራ ላይ በመስፈር ነጋዴዎች ሆኑ።... ጅብላዊ ማለት የተራራ

ስዎች ...ከበርታ ገዢ መደብ አባላት ጋር የጋብቻ ግንኙነት በመፍጠር የገዥነት ስልጣን ለመጨበጥ ችለዋል። ለረጅም ጊዜ ጃብላዊዎች በሼሆች ሲስተዳድሩ ቆይተዋል።...በአባይ ወንዞች አካባቢ የሚኖሩ የበርታ ዝምድ ብድኖች ጋሚለ ...በበርትኛ ቋንቋ የጥቁር ልጆች (Children of Black men) ማለት ነው። የጃብላዊ ብሄረስብ ከጃብላዊኛ ወይም በርትኛ በሁለተኛ ደራጃ ኦሮምኛ፡ አረብኛና አማርኛ ይናገራሉ። ማህበረስቡ ደስታውን የሚገልጽበት የኪነት መሳሪያዎች...አዋዛ ከቀርከሀ በተለያዩ ቅርጾች የሚስራ እንደ አርሞኒካ የሚነፋ፡ እምቡክቡክ የሚባል ከረጅም ሽምበቆ የሚስራ ጎላ ያለ ድምፅ የሚያወጣ...ወዘተ ናቸው።...በጃብላዊ ህብረተስብ ጎጂ ባህል...ጉንጫቸውን፣ ክንዳቸውንና ደረታቸውን የቁንጅና ምልክት ለማድረግ በምላጭ ይተለተላሉ።

የብሄረቡ አጎራባቾች በስሜን ጉሙዝ፡ በደቡብ ማኦና ኦሮሞ፡ በምስራቅ ኦሮሞ፡ በምእራብ ምድረ ሱዳን ናቸው። በታሪካቸው ጃብላዊ ብሄረስብ አንዳንዴ ከኦሮሞ ብሄረስብ ይጋጭ ነበር። ...የብሄረስቡ የህዝብ ብዛት 63256 ነው። በያዘው ስፍራ ኦሮሞ (221,568)፡ አማራ (24,665)፡ ጉመዝ (3,284)፡ ማኦ (13,698)፡ ተስራጭተው ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በ1977-78 በደርግ የስፈራ ፕሮግራም በስግስጋ 1,782፣ በኩታ ገጠም ስፈራ 64,162 የሚሆኑ የተለያዩ የብሄረስብ አባላት ስፍረዋል።

## *7. የሽካቾ ብሄረስብ*

ይህ ብሄረስብ እራሱን ሽካቾ ብሎ ሲጠራ አጎራባች ማህበረስቦች ሞቻና ዋታ እያሉ ይጠሩታል።...የሽካቾ ማህበረስብን በስሜን ምዕራብ መዠንግርና ኦሮሞ፡ በደቡብ መዠንግር፡ በደቡብ ምስራቅ ከፋ፡ በስሜን ምስራቅ እንደገና ኦሮሞ ያገራብቱታል። ከማህበረስቡ ጋር መስባጠር ከፋ፡ ኦሮሞ፡ አማራ፡ ዳውሮ፡ ሽኮ፡ ኮንታና፡ መዠንግር ይገኛል። የብሄረስቡ ቋንቋ "ሽኪ ኖኖ" ተብሎ ይጠራል። የሽካቾ ህብረተስብ አባላት ከከፋ ብሄረስብ አባላት ጋር ያለ አስተርጓሚ ሀሳብ መለዋወጥ ይችላሉ። የህብረተስቡ ኑሮ የተመስረተው በእርሻ ላይ ነው፡ በግብርናው የመኖ ስብልና የገበያ ስብል ያመርታል።

ስለ ብሄረስቡ ታሪካዊ አመጣጥና አስፋፈር በአፈ ታሪክ የብሄረስቡ የተለያዩ ሀሳቦች ይነገራሉ። የመጀመሪያው ከጎጃም አሺውም በላ

ከሚባል ስፈር ባልታወቀ ጊዜ ፈልሰው መጡ፡ ሁለተኛው ከግብፅ ተነስተው የአባይን ወንዝ በመከተል ወደ ኢትዮጵያ ዘልቀው ገሚሱ በጣና ሀይቅ አካባቢ ቀርቶ ወይጦ ተባለ፡ የቀረው ወደ ምዕራብ ዘልቆ በመሄድ ሞቻና ከፋ ላይ ሰፈረ። ሶስተኛው ከረጅም ዘመን በፊት ከትግራይ ፈልሰው በመምጣት በከፋ በሊሙ አውራጃ እናርያ በሚባል አካባቢ መኖር
ጀመሩ። ከጊዜ በኋላ ከእናርያ ገዥዎች ጋር ያለመግባባት ስለተፈጠረ አሁን ወደ አሉበት ስፍራ መጡ ተብሎ ይተረካል። ህብረተሰብ የራሱ የሆነ አስተዳደር ነበረው።…በእናርያ ወይም ሊሙ ቆይታቸው ወቅት ሂኖሮ ታቱ የሚባል መሪ እንደነበራቸውና የሂኖሮ ጭቆና ቀንበር ስለከበዳቸው ታግለው ራሳቸውን ነፃ በማውጣት የራሳቸውን አስተዳደር መስረቱ። የመጀመሪያው መሪያቸው ጋኪ ገጨ ከ 1560-1590 ዓ.ም. እንደገዛ የህብረተሰቡ ሽማግሌዎች ይናገራሉ።

## *<u>የወደፊቱ የአገራችን እጣ ፍንታ</u>*

ለአገራችን ችግሮች የመፍትሔ አሳቦችና መላምት በምናስላስልበት ጊዜ ሁሉንም ጉዳዮች ግልጥልጥ አድርገን ለውይይት ማቅረቡ ጠቀሜታ ያለው ነው። ችግሮቹን ማድበስበሱ አበው እንዲሚሉት “አለባብስው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” እንዳይሆንብን በተለይ የብሄረስብ ችግር አብሮን የኖረና አሁንም ያለ መሆኑን ለመቀበል መቻል አለብን። ብሄረስቦች ተበድለናል ሲሉ ብሶታቸውና ጭንቀታቸው ልንስማቸው ይገባል። የጽንፈኛ አራማጆች ማለት ጠባቦችና ትምክህተኞች ሕዝባችንን ለከፋ ብጥብጥ እየጋበዙት በመሆናቸው ተግባራቸውን አጥብቀን መቃወም አለብን። ጉደኛውና ዘረኛው የወያኔ መንግሥትና የግንጠላ አቀንቃኞች በሚነዙት ውዥንብር ማለት የቅኝ ግዛትነትንና የአገር ግንባታን ፅንስ አሳቦችን አውቀው አንድ አድርገው በማቅረብና ስሜትን በመኮርኮር ችግሮችን በማባባስ ላይ ናቸው። እንደዚህ ያሉ የተለጠጡ የአንድነትም ይሁን የግንጠላ አስተሳስቦች ብዙም የማያስኬዱና በአብዛኛው ሕዝባችን ዘንድም ተቀባይነት የሌላቸው በመሆናቸው ሚዛን የሚደፉ አይደሉም። ለጊዜውም ቢሆን ግን በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ላይ ደንቃራ አልሆኑም ማለት አይቻልም።

ያለፈው አስራ ስባት አመት ተመክሮአችን የሚያስተምረን ያለ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምስረታ የብሄር ብሄረስብ ችግሮችን

ለመፍታት የተሞከሩ ጥረቶች በሙሉ ችግሮችን በመቅረፍ ፋንታ እንዲባባሱ እንዳደረጉ ለመገንዘብ ችለናል። በእኛ እምነት አፍጦና አግጦ ያለውንና የነበረውን የብሄረስብ ችግርና ጭቆና ከመካድ ይልቅ መኖሩን ተቀብለን በጋራ መፍትሔ መፈለጉ ላይ ማተኮሩ ይበጃል ባዮች ነን። ይህን በተግባር እውን ለማድረግ ሁላችንም የአስተሳስብ ለውጥ ማድረግና ከስሜታዊነት መፅዳት አለብን። በስከነ አዕምሮ የፍትህ፡ የስብአዊ፡ መብት፡ የፓለቲካ፡ የኤኮኖሚና የባህል መብቶች እጦትንና እረገጣ በማይዳግም ለማስውገድና የሥር ነቀል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ በጋራ ለማምጣት መታገል ግዴታችን መሆኑን መቀበል አለብን። ከገባንበት የፓለቲካ፡ የኤኮኖሚና የባህል ቀውሶች ለመውጣት ያለን አንድና ብቸኛው አማራጭ ማለትም የወያኔን አምባገነን ሥርዓት ማስወገድና በምትኩ የዴሞክራሲያ ሥርዓት መመስረት ነው።

በእኛ በኩል የህብረብሄር ድርጅት እንደመሆናችን የሚይሳዝነንና ልባችንን የሚያደማው ነገር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከብሄረስብ ብጥብጥ በተጨማሪ የሃይማኖት ልዩነቶች እንዲስፋፉና ልዩነቶች እንዲካረሩ በመደረጉ አገራችን ወደ ባስ አደገኛ ቀውስ እድትገባ እየተገፋች በመሆኑ ነው። የአገራችንም ታሪካዊ ጠላቶች ከገባንበት ቀውስ እንዳንወጣ መስናክል እየፈጠሩብን ነው። ሃያላን መንግሥታትም ወያኔን አቅፈው ደግፈው ለሥልጣን ከማብቃት አልፎ አሁንም በሁለንተናዊ መልክ እርዳታና አለማቀፋዊ ድጋፍ እየተቸረው ነው። ከአለፈው የአገራችን ታሪክ የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር መቼም ቢሆን "እራሳችንን ለማዳን የምንችለው እኛው እራሳችን ብቻ መሆኑን ነው"።

የወያኔ ፍልስፍና ማለት በመጀመሪያ የብሄር ብሄረስቦችን ችግር እንፍታና በኋላ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንሂድ የሚለው ቤተ ሙከራ የማይስራ መሆኑንና ወደ ባስ ቀውስ እንደዘፈቀን ወዳጅም ጠላትም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ለማስታወስ ያህል በ90ዎቹ መጀመሪያ ወያኔ አገሪቱን ተቆጣጥሮ የክልል መዋቅር በሥራ ከመዋሉ በፊት ጥቅሙና ጉዳቱ እንዲጠና የገጠርና ከተማ እድገት-ልማት ባለሙያዎች አሳስበው ነበር። ማን ቢስማ የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተሞች ከመጉረፉ በፊት በከተሞች የሥራ አጥነት፡ የሶሻል አገልግሎቶች ማለት ትምህርት ቤት፡ ሆስፒታል፡ መብራትና ውሃና መኖሪያ ቤት በአጥጋቢነት መስጠት ያልተቻለበት ነበር። የገጠሩ ሕዝባችን ወደ

ከተሞች ተገዶ መፍለስ ለከተሞች በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ ሆነ። በከተሞች በተለይ አዲስ አበባ ሕዝብ የተጨናነቀበት የኑሮ ውድነት፣ የመኖሪያ ቤትና የሥራ እጦትና የማህበራዊ አገልግሎት ማለት የመብራት አገልግሎት በፈረቃ የሚሰጥበት ማለት በሁለትና በሦስት ቀን አንድ ጊዜ የሚዳረስበት እንዲሁም የውሃ እጥረት ያለበት ሆኗል። በአጭሩ በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ ከወያኔና ከተለጣፊ ሹማምንት ማለት ካድሬዎችና ወዶገብ ሆዳሞች በቀር ሕዝባችን በስው ስራሽ ርሃብ፣ ፍትህ አልባነትና ስብአዊ መብቱ በመረገጥ በምድር ላይ ሲኦል ውስጥ የሚኖር ሆኗል። ታዲያ እስከመቼ ነው ይህ ግፍና መከራ የሚቀጥለው? እውነትም እንደተባለው “ሽክም የማይከብደን” ሕዝብ ሆነናል ማለት ነው? መልሱን ህሊናቸው ከሆዳቸው ለማይቀድምባቸው አንባቢያን እንተወዋለን። ግን አንድ ማስረገጥ የምንፈልገው ጉዳይ ወያኔን የምር እንታገላለን ለምትሉ ወያኔ ጠላት ነው ስለዚህ በሁለገብ መንገድ ከመታገል በቀር ሌላ አማራጭ አለመኖሩን መቀበል መቻል እንዳለብን ነው።

እግዚኦ መሐረነ የሚያስኘው የዘረኛው ወያኔ መንግስት ከጎንደርና ከወሎ መሬታቸው ተቆርሶ ለትግራይ ክልል እንዲሆን አድርጓል። ይህ አልበቃ ብሎት የዘረኛው ወያኔ መንግስት አሁን እንደምናየው ዳር ድንበራችንን አስደፍሯል። በምዕራብ ከሱዳን ጋር የሚያዋስነንን እርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ከ 30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሚሆን መሬት ማለት ከጎንደር፣ ከወለጋና ጋምቤላ ውሃ ገብ ለም መሬትና
እምቅ ነዳጅ ክምችትና ማዕደናት አሉባቸው ተብለው የሚገመቱትን ለሱዳን በገፀ በረከትነት ስጥቷል። ያካባቢው ሕዝቡም ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ከፊለፊት ከሱዳን ሠራዊት ከበስተጀርባ ከአጋዚ ጦር የሚሰነዝርበትን ጥቃት በመከላከል ይገኛል። ከቦታቸው ከአጽመ እርስታቸው እንዲፈናቀሉና እንዲሰደዱ ከእያቅጣጫው ጫና እየተደረገባቸው ነው። ከሁሉ ሁሉ የጉድ ጉድ የሚያስኘው ነገር መቼም ከስንዴ መካከል እንክርዳድ አይጠፋምና አገራችን በክልል ከመሸንሸኑ አልበቃ ብሎት፣ አንድ ጥይት ሳይተኮስ ለኢትዮጵያ ጥቅምና ህልውና ደንታቢስ የሆነው ዘረኛው ወያኔ በምዕራብ ጠረፍ በኩል ለሱዳን የስጠው መሬት አፄ ዮሐንስ መስዋዕት የከፈሉበት፣ አፄ ቴዎድሮስ ተወልደው ያደጉበትን ቋራንና እንዲሁም ለም መሬት የሆኑትን መተማን፣ ሁመራን፣ እንዲሁም ከአርማጭሆ እስከ ጋምቤላ ያለውን በገፀ በረከትነት ለሱዳን መስጠቱ ነው። ይህን ሁሉ በትግራይ ሕዝብ ስም

መፈጸሙ ያሳዝናል። አዬ የዚያ ትውልድ ፈርጦች አባል የነበረው ጓድ ሃይለ ሥላሴ ገብረ መስቀል የቀይ ሽብር ሰለባ የሆነው፣ የትግራይ ተወላጅና የኮተቤ የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጅ መምህር በሕይወት ኖሮ ቢሆን ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም ይህን ሁሉ በደል መፈጸሙ ምንኛ በአሳዘነው ነበር። እሱ ግን የበኩሉን ብሄራዊና ድርጅታዊ ግዳጁን ተውጥቶ በመስዋዕትነት አልፎአል።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ አገራችን አሁን በትልቅ አደጋ ላይ በምትገኝበት ሰዓት "ዘመናዊና ሁሉን አዋቂ" ፕሮፌሰሮች መካከል አንዱ ውድ ጊዜያችንን በአላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ እንድናጠፋ ሙከራ አድርጓል። ለነገሩማ እነዚህ ዘመናዊ ሥልጡን ወቃሾች ተማሪ እያሉ የፊውዳሉ ሥርዓት አቀንቃኞች የነበሩ ማለት በኢትዮጵያ የመደብ፣ የሃይማኖትና የብሄረሰብ ጭቆናና በደል አልነበረም ባዮች ነበሩ ናቸው። የግራ ዝንባሌ የነበራቸው ተራማጅ ተማሪዎች ደግሞ ሕዝባችን ተበድሏል፣ ፍትሕ ተጓደለ እድገታችን አዝጋሚ ሆነ እንዲሁም በገበሬው በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚደርስበትን ግፍ ለማቆም "መሬት ለአራሹ" ይስጥ ብሎ፣ በኋላም በኢሕአፓ መሪነት በደርግ ዘመን ዴሞክራሲ ያለገደብና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ወዘተ መፈክሮች ስር ታግሏል ሕዝባችንንም አታግሏል።

አሁን ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነና ታዲያ "ላም ባልዋለበት ኩብት ለቀማ" ሆኖ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጣታቸውን በኢህአፓ ላይ መቀስርና በሀስት መክሰስ ሥራችን ብለው ተያይዘውታል። በተለይ በአሁኑ ወቅት አገራችን በአደጋ ውስጥ በምትገኝበት ጊዜ በእንደዚህ ያለ ፋይዳቢስ ነገር ከመጠመድ ይልቅ ፓርቲው በሂደት አስተካክሎ የደረሰበትን አቅዋሙን በልሳኑ በዴሞክራሲያ በግንቦት 1994 ያወጣውን ልዩ እትም "ኢህአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ" ቢያነቡና ባለማወቅ ከሆነ ከሚፈጸሙት ውዥንብር መንዛት፣ አድርባይነትና ቅጥረኝነት ተግባራቸው ታቅበው፤ ለጥፋታቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ አገር ማዳኑና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ መሳተፉ ይበጃቸዋል
ብለን እንመክራለን። ከዚህ ውጭ "በሬ ወለደ" ማለቱ በአውቆ አጥፊነት የሚያስፈረጅና ወደፊትም በትውልድና በታሪክ በወንጀለኛነት የሚያስጠይቅ ነው እንላለን።

ደርግም "በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ" አይነት ሆኖበት እድሜውን ለማራዘምና ያለበትን ውጥረት ማለት የብሄር ብሄረሰብ ጥያቄ ለማርገብ ፌደራል
መስል "ከፋፍለህ ግዛ" መዋቅር አዘጋጅቶ ነበር። መዋቅሩም አምስት የራስ ገዝ (autonomous regions) ማለት እንደ ኤርትራ፥ ትግራይና የአሰብ አስተዳድር ችግር ያለባቸውን አካባቢ እንዲሁም ቀሪውን ስላሣ ስድስት የአስተዳደር ክፍሎች ብሎ (administrative regions) አዋቅሮ ነበር። ለአብነት ከአስተዳደር ክፍሎች መካከል ጎንደርን በሁለት ማለት ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፥ ሸዋን በአራት ክፍሎ ነበር። ወያኔ ደግሞ በተራው በቋንቋ ላይ ብቻ የሙጥን በማለት ሸዋን ለሁለት ክፍሎ ሰሜን ሸዋን ወደ አማራ ክልል ሲያስገባ፥ ደቡብ ሸዋን ወደ ኦሮሞ አካልሎአል። የክልል ሹማምንትም ተብዬዎች የወያኔ ተለጣፊዎች በመሆናቸው የወያኔ ሕገመንግስት የሚፈቅደውን መብት ለክልላቸው ለመጠየቅ ድፍረቱና ብቃቱም የላቸውም። ዘረኛውም የወያኔ አምባገነን መንግሥት በተለጣፊዎች መስሪ ተንኮል ለምሳሌ የኦሮሞንን ሕዝብ ከአማራ፥ ከአፋር፥ ከሱሜሌ እንዲሁም ከቀሩት አጎራባች ብሄረሰቦች ጋር በመሬት ይገባኛልና በድንበር እንዲጣላ እንዲሁም በኦሮሞ መካከል ወደ ጎሳ ወርደው ለምሳሌ በጉጂና በቦረና ህብረተስብ መካከል በወያኔ ካድሬዎች ጠብ ጫሪነት አንዱን በማስታጠቅና ሌላውን ትጥቅ በማስፈታት ብዙ ሕይወትና ንብረት እንዲወድም እየተደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በስው ስራሽ ርሃብና በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ነው። በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የዚህኛውና የዛኛው የተቃዋሚ ደጋፊ ናችሁ በመባል በእስር ቤቶች ታጉረውና ያለፍላጎታቸው በስደት በጎረቤት አገሮች ማለት የወያኔ ሽሪክ ከሆኑት አገሮች ውስጥ በአስቃቂ ሁኔታ ይገኛሉ። ለማጠቃለል ሁለቱም አምባገነን መንግሥስቶች ማለት ደርግና ወያኔ ያልገባቸው ወይም ለመረዳት ያልቻሉት አንድ ነገር ቢኖር በአንደኛው ክፍለ ዘመን ምንም ዓይነት ፌደራሊዝም ይሁን ልማት ያለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሕዝብ ይሁንታ ፋይዳቢስ መሆኑን ነው። በጊዜው ደርግ በጉልበት ያሻውን አድርጓል፡፡ አሁንም ወያኔ ያሻውን እያደረገ ይገኛል። ሁሉም የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ከሕዝባዊ ቁጣ አያመልጡም።

## የብሄረሰቦችን ባህላችንና ቋንቋዎች ለማዳበር ጥቆማዎች

በአገራችን ስር ነቀል ሥርዓት ለውጥ ለማምጣት እንደ ፖለቲካና ኤኮኖሚ ትግል ሁሉ የባህል ተሃድሶ ማድረግ ወሳኝና አስፈላጊ ነው።

ጎጂ ባህሎቻችንን አስወግደን መልካሙን የማዳበር ግዴታ አለብን። ለምሳሌ የማይሰራው ሳይሆን የሚሰራው ገበሬው፡ አንጥረኛው፡ አዝማሪው፡ ላብ አደሩ…ወዘተ መከበርና መሞገስ አለበት። የብሄረሰቦች መልካሙ ባህሎችና ቋንቋዎች መዳበር በቃልም በተግባርም መደገፍ አለበት። ይኸ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ አገር የሚኖሩ ብሄረሰቦች የሚገናኙበትና የሚግባቡበት አንድ ብሄራዊ ቋንቋ ያስፈልጋቸዋል። ይህም ጎን ለጎን የብሄራስብችን ቋንቋና ባህል በማይገድብ መንገድ ቢያንስ እንደ አንድ ትምህርት አማርኛ (as one of subject matters) መስጠቱ አስፈላጊ ነው። በአንድ አገር የኛን የመሰለ ባለብዙ ብሄረሰብ ሁሉን ሊያገናኝና ሊያስማማ የሚችል አንድ ብሄራዊ ቋንቋ አስፈላጊ መሆኑ ብዙ አያከራክርም። የብሄራዊ ቋንቋ በዘፈቀደ የሚለዋወጥ አይደለም በሂደት በረጅም ጊዜ የሚዳብር ነው። "ከታሪካችን ለአብነት ለመጥቀስ ዮዲት በነገሰች ጊዜ ብሄራዊ ቋንቋችን እብራይስጥ እንዲሆን አላደረገችም፡ ኢማም አህመድ መሀመድ ሥልጣን ሲይዙ አረብኛና አፄ ዮሐንስ ትግርኛ እንዲሆን አላደረጉም፡ ሁሉም መንግስታት የአስተዳደር ቋንቋው አማሪኛ እንዲሆን ነው ያደረጉት" (ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ ጽሁፎች የተወሰደ)። አብዛኛዎቹ የውጭ አገር ተመራማሪዎች ግዕዝ ሴማዊ ቋንቋ ነው ማለት እንዲህ ያለ ጥቁር ሕዝብ የራሱ ፊደልና ቁጥር ያለው ቀመር ሊያመነጭ አይችልም። በዘረኝነት ወይም በሌላ ምክንያት አዋቂዎቹ ከውጭ የመጣ መሆን አለበት የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ይመስላሉ። የግዕዝ ቋንቋና ፊደል አንዳንድ ሊቃውንት ኢትዮጲስ ብለው የሚጠሩት ምንጬ ከእስያ ማለት የሴማዊ ቋንቋ ነው ተብሎ በተለምዶ በተለይ በፈረንጆቹ የታሪክ ተመራማሪዎች በስፋው ብዙ መጻሕፍት ጽፈው አለምን ለማሳመን ብዙ ጥረቶች ይደረጉበት ጉዳይ ነው። በቀድሞው አስተሳሰብ የአለም ስልጣኔ፡ የሰው ዘር ምንጬና ቋንቋዎች የፈለቁበት በእስያ ለአብነት በጥንታዊ በርሽያ፡ በኢፍራትስና ጥግሪስ ወንዞች አካባቢ እንዲሁም በህንድ፡ በጋንጅስ ወንዝ ዳርቻ ነበር ተብሎ ስለሚታመን ነበር ማለት ይቻላል። በእርግጥም የተጠቀሱት አገሮች ለአለም ያበረከቱት አስተዋፆ የሚደነቅ ነው።

ጥንታዊ ኢትዮጵያም በአንድ በታሪክ ወቅት በዘመኑ ከሚጠቀሱ ታላላቅ አገሮች ማለት ህንድ፡ ቻይና ፐርሽያ መደዳ የምትጠቀስ አገር እንደነበረች ታሪክ ይመሰክራል። በአባይ ወንዝ ዳርቻም ለዳበረው ሥልጣኔ ኢትዮጵያ ከጥንታዊ ጥቁር ግብጾች ጋር ተጋሪ እንደነበረች ታሪክ ይመሰክራል። አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን አዳዲስ ግኝቶች

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ነች እስከመባል የተደረሰበት ጊዜ እንገኛለን። ኢትዮጵስ ከኢትዮጵያ የተፈጠረ አፍሪካዊ ቋንቋ ነው የሚል ምርምሮችን የሚያደርጉ የአፍሪቃ ቋንቋ ተመራማሪዎች እንደ ፕሮፌስር አየለ በክሪ አይነቶች ብቅ እያሉ ነው። አማርኛና ትግርኛ የፈለቁት ከግዕዝ ነው፡ ከዚያ በላይ በኤርትራ ቆላማው አካባቢ የሚኖሩ ትርገኛ ቋንቋ የሚናገሩት ከግዕዝ ጋር በጣም የሚቀራራቢነት ያለው ነው።

በዘመናችን የአፍሪካ ቋንቋዎች ተመራማሪዎች እንደነ ፕሮፌስር አየለ ያሉ ግዕዝ
ሳባዊ ሳይሆን አፍሪካዊ ቋንቋ ነው በማለት ጥናቶች በማካሄድ ላይ ናቸው። ትልቁ ሥራቸው ኢትዮጲስን (Ethiopic Writing System) የፊደል ቀመሩ ወደ ጎን ሰባት ወደታች ሃያ ስድስት በድምሩ 182 ሆሂዎች መሆናቸውን ማብራራት ላይ ናቸው። ሌላው ግዕዝን ከላቲን ቋንቋ ጋር ጥቅሙንና ጉዳቱ በማወዳደር፤ ግዕዝ ማለት ኢትዮጲስ ለአፍሪካ በተለይም ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የማንነታችን፡ የታሪካችንና የባህላችን እንዲሁም የፍልስፍናችንና የሳይንስ ምርምር ለምሳሌ የከዋክብት ቆጠራ መግለጫችን ነው። ኢትዮጲስ አፍሪካዊ ቋንቋ የሆነና ለዓለም
ህብረተሰብ ታላቅ ታሪካዊና ባህላዊ ግኝታ አስተዋፆ ያበረከተ ነው። አሁን በመነገር ላይ ያለው የአማርኛ ቋንቋ የየትኛው ብሄረሰብ የግል ቋንቋ ሳይሆን የብዙ ብሄረቦች ቃላት ያካተተ ለምሳሌ ያሀል ጨጨብሳ፡ አቴቴ፡ ጨሌ ወዘተ…የኦሮምኛ ቃላቶች ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪ በአብዮታችን ጊዜ ሁኔታውን ለመግለጽ የተፈጠሩ ቃላት በርካታ ናቸው። ከውጭ ቋንቋዎች ውስጥም አረብኛ፡ እንግሊዝኛ፡ ጣሊያንኛ ቃላቶች ወዘተ ይገኙበታል። በአጠቃላይ አሁን በከተማ የሚነገረው አማርኛ በተለይ በሬዲዮኖች የሚነገረው ለገጠሬው ሕዝባችን ግር የሚል ደረጃ የደረሰበት ወቅት ደርስናል። ስለዚህ በታሪክ አጋጣሚ አማርኛ የብሄራዊ ቋንቋ ሆነ እንጂ ሌላው በዳበረ ጊዜ ብሄራዊ ቋንቋ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ይህ ወደፊት በሂደት የሚሆን ጉዳይ ነው።

የአገራችንን ህልውና የማንነታችን ምልክት ማለት ስንደቅ አላማችንና ኢትዮጵያዊነታችን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አውዳሚ አቅጣጫ እያመራን መሆኑ ነው። በዚህ በአስራ ሰባት አመታት የተከሰተ ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ የፓለቲካ ትግል ውስጥ ማን ምን እንደሆነ ፍንተው

ብሎ የታየበትና የታወቀበት ነው። ማን ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም እንደቆመ፡ ማን ለስር ነቀል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት እንደሚታገልና ማን ለጥገናዊ ለውጥ እንደሆነ እንዲሁም አንጃኛ፡ አድርባይና ቅጥረኛ እንነማን እንደኑና ከጠላት ጋር እንደሚስሩ ለሕዝባችን ግልጥልጥ ብሎ የወጣበት ጊዜ ነው። ከምርጫ 97ቱ በፊት ብዙ አስመሳዮች "በሩ ገርበብ ብሎአል"፡ "በሩ ተከፍቶአል" እያሉ ለማወናበድ የሚሞክሩበት በር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እስከፍጻሜ ወያኔ የተቸነከረ መሆኑን ሕዝባችን ስለተረዳ፤ እንዳለፈው ጊዜ ግራ የመጋባት ወቅት ያከተመበትና የሥርዓቱን በር በሕዝባዊ አመፅ ሰባብረን መክፈት የእኛ ሃላፊነት ነው። በምህላና በልመና የሚመጣ ነገር የለም። በመሆኑም የትግላችን መርሆ ግለጽና አሻሚ ያልሆነ ማለት የዘረኛውን የወያኔ መንግሥት በሁለ ገብ ትግል አስወግደን በምትኩ ስር ነቀል የዴሞክራሲያ ሥርዓት በአገሪቱ ማስፈን ነው። ለዓላማችን ስኬታማነት አስፈላጊ የሆነውን መስዋዕትነት ለመክፈልም ዝግጁ ነን።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታም ወቅት ማለት በሽግግር ጊዜ ሁሉንም የህብረተስብ ክፍሎች የሚያካትት የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አማካኝነት ያገሪቱን
ችግሮች በሁለንተናዊ መልኩ መርምሮ የመፍትሔ አሳቦችን እንደልብ ተንሽራሽረው፤ በውይይት፡ በክርክርና፡ በመተማመን ስምምነት ላይ መድረስ አለብን። በዚህ ቅድመ ዝግጅት ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ "የእኔ ነው" ብሎ የሚቀበለውና የሚያከብረው እንደአይኑ ብሌን የሚንከባከበውና የሚጠብቀው የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግስትና ሥርዓት ለማዘጋጀት ምቹ ሁኔታ ይፈጠርለታል ማለት ነው። በሕገ መንግሥት ማረቀቅና ማጽደቅ ሂደት ውስጥ ሕዝባችን በተወካዮቹ አማካኝነት መክሮበትና ክሮበት በሥራ ላይ እንዲውል ይሁንታውን ሲስጥ ያኔ የሁሉም ዜጋ
"የቃል ኪዳን" ውል ይሆናል ማለት ነው። በእኛ በኩል በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማንኛውም ችግር በየደረጃው ተፈትቶ ለሁሉ የምትሆን ዳር ድርበሯ የተከበረ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ኢትዮጵያ ትመስረታለች የሚል ጠንካራ ተስፋ/ጉጉት ያዘለ ራዕይ አለን። ይህን ራዕያችን እውን ለማድረግ የሚጠበቅብንን መስዋዕትነት በመክፈል ማለት በሁለገብ መንገድ መታገል መርሆአችን ነው። ሕዝባችን ከአለበት አስቃቂ ቀውስ ለማውጣት በኦሮሞ ወይም በሌሎች ስም የተደራጃችሁ የብሄረሰብ ድርጅቶች የተደቀነብንን ወይም የተደገስልን ውድመት በጽሞና

መርምረው በጋራ የዘረኛውን የወያኔ አምባገነን አገዛዝ አሽቀንጥረን ጥለን በምትኩ የዴሞክራሲያ ሥርዓት በመመስረት ችግራችን ፈተን ለሰላም፡ ለልማትና ከድህነት ለመላቀቅ በጋራ እንታገል የሚለውን ቀዋሚ ጥሪያችን እናስተላልፋለን። ትግላችን አንድነቷ የተጠበቀ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክን መመስረት ነው።

የሁሉም የብሄር ብሄረሰቦች የግልና የብድን የስብዓዊ መብት መከብር፡ የመስብሰብ፤ የመደራጀት፤ በነፃ አሳብን ማንሸራሸር እንዲሁም በአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚና የሶሻል ኩልነት የሰፈነበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ነው። ይህን የተቀደሰ ዓላማችን ከግብ ለማድረስ በሕይወት እስካለን ድረስ በሁሉም ዘርፍ እንደምንታገል ቃል እንገባላችኋለን።

በመጨረሻም ለወጣቱ ትውልድ ማስተላለፍ የምንፈልገው ጉዳይ የአገራችሁን ታሪክ የተጻፉትንና በቃል የሚነገሩትን አጥኑ በግልም ሆኖ በቡድን ከምተማመኑት ጓደኞቻችሁ ጋር ሆናችሁ አንብቡ፡ ተመራመሩና አሳባችሁን በወረቀት ላይ አስፍሩ እንዲሁ የመናገር ችሎታችሁንም አዳብሩ። ከእኛ ተመክሮዎች ተማሩ አሉታዊውን ላለመድገም አዎንታዊውን ለማዳበር ጥረት አድርጉ። ለሁሉም እንበርታ።


## *ዋቢዎችና ማብራሪያዎች*

1- ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1961 ዓ.ም 4ኛ እትም፤
2- ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ 1936 ዓ.ም፤
3- እንደ አቶ ተክለ ጻድቅ ማብራሪያ በኦርቶዶስ ቤተ ክርስቲያን በሊቃውንት መካከል የተከሰተው ልዩነት፤

- ክርስቶስ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ነው፡ ተዋህዶ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ የኛን ሥጋ በአካሉ ከፍሎ ቢዋሀደው በስውነቱ እንደ አብ እንደ መንፈስ ቅዱስ ያለ ፍጹም አምላክ ሆነ የሚሉ ተዋሕዶዎች ናቸው።

- የሥጋና የቃል መዋሀድ ሁለትነትን አጠፋ እንጂ ቃል የለበሰውን ሥጋ የባሕርይ አምላክነት ክብር ያከበረ መንፈስ ቅዱስ ነው የሚሉ ቅባቶች ናቸው።

- ቃል በለበሰው ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ እንደኛ የጸጋ ክብር አግኝቶ ክርስቶስ ተባለ የሚሉ የጸጋ ልጆች ናቸው።

4- በጎንደር ቤተ መንግሥት በነገስታቱ ስም አገሪቱን የገዙ መሳፍንት ስም ዝርዝር።

- ራስ አሊ ትልቁ 1777-1781
- ራስ አሊጋዝ 1781- 1786
- ራስ አሥራትና ራስ ወልደ ገብርኤል 1786-1792
- ራስ ጉግሳ 1792-1818
- ራስ ይማም 1818-1820
- ራስ ማርዬ 1820-1823
- ራስ ዶሪ 3 ወር
- ራስ አሊ ትንሹ 1823-1845

5- ተሻለ ጥበቡ፡ Making of Modern Ethiopia
6- ዴሞክራሲያ "ኢህአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ" ልዩ ዕትም ግንቦት 1994
7-የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት፡ አጭር የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ማውጫ ህዳር 1978
8-Berhanu Gutema Balcha, Ethnicity and Restructuring of the State in Ethiopia, DIIPER Research Series, Working Paper No.6
9- http://jimmatimes.com Historical Analysis & Synthesis, 2007